

የሀገራቸውን ድንበር ከወራሪ ለመጠበቅ በእጃቸው
የተገኘውን መከላከያ ይዘው ጎጇቸውን ዘግተው
ወጥተው ለቀሩ ኢትዮጵያውን መታሰቢያ

የኢትዮጵያውያን ዘማቾች ሰልፍ በአዲስ አበባ በመጀመሪያው ገፅ ላይ የሚገኘው ፎቶግራፍ ጦርነቱ ሲጀመር አዲስ አበባ በነበረ በእንግሊዝ አገር የደይሊይ ሜይል ጋዜጣ (Daily Mail) ፎቶአንሽ የተነሳ ነው፡፡ ከደይሊ ሜይል ላይብራሪ የተገኘ (በሴባስቲያን አኬሊ አማካኝነት)



# (የተደበቀው ማስታወሻ)

(የ1928-1929 ዓ.ም የኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነት መዘከር)

በዶክተር ሀራልድ ናይስተሮም

የአማርኛ ትርጉም
ዶክተር ገበየሁ ተፈሪ
ደስአለኝ አለሙ

ሁለተኛ እትም
ጥቅምት 2007 ዓመተ ምሕረት
October 2014

WITH ST. GEORGE ON THE DEATH RIDE
*A Memoir of the Italian-Ethiopian war of 1935-36*
Dr. Harald Nystrom

English Translation
Dr. Thomas P. Coleman
April 2012

Amharic Translation
Dr. Gebeyehu Teferi
Dessalegn Alemu
June 2014

ሁለተኛ እትም ጥቅምት 2007
Second edition October 2014
Signature Book Printing, www.sbpbooks.com

በዚህ በሁለተኛው እትም የትርጉሙ ፅሁፍ ላይ ከፊደላት እርማት በስተቀር ምንም አይነት ለውጥ ያልተደረገ ሲሆን ለፅሁፉ ምስከርነት የሚሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በመፅሐፉ ውስጥ የጨመርን መሆኑን ለማስታወቅ እንወዳለን:: በኛ በኩል የቀረቡ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በገፆች ግርጌ ሠፍረዋል:: ብዙ አንባቢዎች የለገሡንን ምክር በመስማት ሽፋኑ ላይ የመፅሐፉን ይዘት ለመግለፅ ተጨማሪ ፅሁፎችና ምስሎች ጨምረናል:: ስለዚህ ከዚህ ቀደም በመጀመሪያው እትም በሞት ጉዞ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋራ በሚለው የመፅሀፉ ርእስ ላይ ተጨማሪ ገላጭ ርዕስ መጠቀማችንም ለመግለፅ እንወዳለን:: በዚህ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙ ፎቶግራፎችና ምስሎች ከፀሐፊው ፎቶግራፍ ውጭ በትርጓሚዎች የተሰበሰቡና የተዘጋጁ ናቸው:: የመፅሀፍ ሽፋን ዲዛይን በገበየሁ ተፈሪ

Copy right © 2014 by Gebeyehu Teferi & Dessalegn Alemu
የገበየሁ ተፈሪና ደስአለኝ አለሙ ሙብት በህግ የተጠበቀ ነው በጽሑፍ በተሠጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር መፅሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተም መቅዳት መባዛት ወይም ሙተርጎም አይቻልም::
All rights reserved including the right of reproduction in whole or in part in any form.

Chibo Light Book
ISBN 9780692268933
Second Edition
www.chibolight.com
Info@chibolight.com



ለ/To ____________________

____________________

____________________

ከ/From ____________________

# ምስጋና

የእንግሊዝኛውን ፅሁፍ (With St. George on the Death ride) ወደ አማርኛ እንድንመልስ ስለፈቀዱልን ለጁዲት እና ክርስቲን ፒተርሰን ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

ተጨማሪ መረጃዎችን እንድናገኝ ለተባበሩን የላይብራሪ ኦፍ ኮንግሬስ ባልደረባ (Library of Congress) ለሆኑት ለአቶ ፋንታሁን ጥሩነህ ከልብ ምስጋና እናቀርባለን

በዳባት ከተማ በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙ መረጃዎችን ለማግኘት ለረዱን ለወይዘሮ ላንቸስል አለሙ ምስጋና እናቀርባለን

ለመፅሀፉ ታላቅ ድጋፍ የሀሳብና ሌሎችም ርዳታ ላደረጉልን ለፕሮፌሰር ሀይሌ ገሪማ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

መፅሐፉን በሚመለከት ላበረታቱንና ለረዱንና ጠቃሚ ምክሮችን ለሰገሡን በሙሉ ምስጋና እናቀርባለን

የመጀመሪያውን የመፅሐፍ ግምገማ በመኖሪያ ቤታቸው ላዘጋጁት የቅርብ ጓደኞች ከፍተኛ ምሥጋና እናቀርባለን፡፡

ከሁሉም በላይ ግን እንደዚህ አይነት ዘገባ በማስቀመጥ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረጉት ፀሐፊው ዶክተር ሀራልድ ናየስተሮምን በራሳችን በመላው አንባቢ እና በኢትዮጵያውያን ስም እናመስግናለን

የስዊድንኛ ቋንቋውን ወደ እንግሊዘኛ በመመለስ ይህንን ያልታየና ያልተሰማ ፅሁፍ ለአማርኛ አንባቢዎች እንድናቀርብ ትልቅ ምክንያት ለሆኑት ለዶክተር ቶማስ ፒ ኮልማን በራሳችን በመላው አንባቢ እንዲሁም በኢትዮጵያውን ስም ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

በዚህ እትም ለታሪኩ ከፍተኛ ማስረጃ ሆነው የተገኙ ፎቶግራፎች የተገኙት ሴባስቲያን አ ኬሊ ከፃፉት መፅሐፍ ነው፡፡ ሴባስቲያን አ ኬሊ (Sebastian O'Kelly) ደግሞ ያለምንም ማመንታታት ፎቶግራፎችን እንድንጠቀም ስለፈቀደሉን ጥልቅ ምስጋና እናቀርባለን

ከጎናችን በመሆን በማበረታታት ለረዱን ለባለቤቶቻችን የልብ ምሥጋና እናቀርባለን

ዶክተር ገበየሁ ተፈሪ
አቶ ደስአለኝ አለሙ



# ከተርጓሚዎች

*ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ*

እንደሚባለው እንደዚህ ጥርት ያለ በቀናትና በሰአታት የተደገፈ በቦታው በነበረ ሰው የተፃፈ ማስታወሻ ማግኘት ቀላል አይደለም፡፡

በመጀመሪያ እንዲህ አይነቱ ፅሁፍ ለአንባቢ እስካሁን ሊደርስ ያልቻለበትን ምክንያት ወይም ለምን አሁን የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነው፡፡ የማስታወሻው ባለቤት ፀሀፊው በስዊድን ቋንቋ ከዚህ በፊት በ1938 (እኤአ) አሳትመው ከዚያ ወዲያ ግን ዶክተር ሀራልድ ናየስተሮም በሕይወት እያሉ ፅሁፉ በእንግሊዝኛም ሆነ በአማርኛ እንዳይተረጎም ከልክለው ከሞቱ በኋላ ግን ፅሁፉ ለአንባቢያን እንዲደርስ ስለፈቀዱ ነው፡፡ ፀሐፊው ይህንን የመሰለ ዘገባ ለአንባብያን እንዳይደርስ ያደረጉበት ለኛ ግልፅ ባይሆንም በቂ ምክንያት ነበራቸው፡፡ ስለዚህ ፀሐፊው ከሠጡት ርዕስ መውጣት ባንፈልግም ለፅሁፉ ተስማሚ ገላጭ ቃል "የተደበቀው ማስታወሻ" የሚል ተደራቢ ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡

ዶክተሩ በሞት ሲለዩ ጓደኛቸው ዶክተር ኮልማን ፅሁፉን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመው ያጠናቀቁት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 ነበር፡፡ እንግዲህ ፀሐፊው ለምን ፍራቻ እንዳደረባቸው ከፅሁፉ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ዶክተር ናየስተሮም የአማርኛ ቋንቋን በደንብ ይናገሩና ይፅፉ ስለነበር በጊዜው የተደረገውና የተነገረውን ነገር ያለምንም አስተርጓሚ እንዳለ ማስቀመጣቸው ሌላው የፅሁፉ ጠቀሜታ ነው፡፡

በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ስለተደረገው ጦርነት ብንሰማም ምን አይነት ባህሪ እንደነበረው ከዚያም ከውጊያ አልፎ ጭፍጨፋ ላይ ያተኮረና ያጋደለ ጦርነት መሆኑን ምን ያህል ሰው በውል ያውቅ ይሆን? እኚህ ሰው ወደ ጦር ሜዳ ግንባር ተጉዘው በቦታውም ሆነው የፃፉት ስዕላዊ አገላለጥ ትልቅ የታሪክ ቅርስ ነው፡፡

አንባቢዎች ወደፊት እንደሚረዱት ፀሐፊው ሚዛናዊ የሆነ አቀራረብ ነው ያላቸው፡፡ ደግሞም ግን በጊዜው ያዩትና የሰሙትን ነው የፃፉት፡፡ ፈሪውን ከጀግናው ጋራ፤ ተንኮለኛውን ንፁህ ልቦና ካለው ሰው ጋራ እኩል ነው ያቀረቡልን፡፡

ሌላው የዚህ ማስታወሻ አቢይ ነገር "አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" እየተባለ እስካሁን ድረስ የሚዘፈንላቸውን ደጃዝማች አያሌው ብሩን ከጎናቸው አብረው ውለው አድረው ያሰፈሩት ማስታወሻ ለአያሌው ሞኙ መዘፈን ምክንያት ከደጃዝማቹ ከራሳቸው እንደበት የሰሙትን መረጃ ይጨምራል።

እንግዲህ ፀሀፊው የሰዎችን ስሞች እየጠቀሱ በዚያን ጊዜ የተደረገውንና የተባለውን ያዩትንም በመዘገባቸው ደጉንም ከፉውንም ለይተው በመፃፋቸው ለብዙ ሰማቸው ለተጠቀሱ የዚያን ጊዜ ከፍተኛ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናች ቤተሰቦችን ቅር ሊያሰኝ የሚችል ነገር ሊኖር እንደሚችል ይገባናል። ሆኖም መተርጎም እንጂ ማብራራት ወይም ሌላ ጭማሪ ስልላተደረገበት የሆነውን መቀበል የግድ ነው።

በተጨማሪም ታሪክ ወይም ያለፈ ማስታወሻ ሰዎች እንዳያዝኑ ወይም እንዳይቀየሙ ተብሎ የሚዛመም ከሆነ ከእውነታው ይርቃል። ልጅን ሲወዱ ከነ እንትኑ እንደሚባለው ታሪክን ሲቀበሉ ደግሞ ከነእውነታው መሆን አለበት።

ማስታወሻነቱ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለነበረው ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ለተሰራው ድርጊት በኋላም ለወደኋላ ለታየው ሁኔታ መንሰኤ ጥቆማ ያበረክታል። እያንዳንዱ አንቀፅ በፅሞና ሊነበብ የሚገባው ማስታወሻ ነው። አቀራረቡ ሰእላዊ መግለጫ ሰለሚሠጥ አንባብያንን እንደሚመሥጥ እርግጠኛ ነን።

ትርጉም ሰለሆነ እንደተፃፈውና የማስታወሻው ባለቤት ሊገልጡት እንደፈለጉት አድርገን አቅርበናል። በፅሁፉ ውስጥ ግን አንዳንድ የቃል አጠቃቀሞችን የግድ መቀየር ተገደናል። ለምሳሌ ባሪያ ወይም ባሪያዎች የሚለውን ቃል በአገልጋዮች መተካታችን ለአንባብያን ማስታወስ እንወዳለን።

ፈሪዎችንና ተንኮለኞችን እንደዘገቡት ሁሉ በማስታወሻቸው ያሰፈሯቸው የኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች ሰዕላዊ አገላለፅ ለምናውቀውና ለሚነገርለት የኢትዮጵያውያን ጀግንነት በቂ መረጃ ነው። ጀግንነቱ ደግሞ ከተራው ሰው እስከባላባቱና ካህናቱንም ጨምሮ ነው። የተዋጋው የኢትዮጵያ ወገን ከየቦታው ከተት ብሎ የወጣ ነው። ጎጇቸውን ዘግተው ሴትና ልጆች ባሎቻቸውን አባታቸውን ቢቆሰል ሊያስታምሙ ቢሞት ደግሞ ሊቀብሩ ተከትለው ወጥተዋል። በማስታወሻው የከምባታ ተወላጆች የሰሩትን የጀግንነት ሥራ ማንበብ የሚያኮራ ሆኖ አግኝተነዋል።




ይህ ማስታወሻ ለታሪክ ባለሙያተኞች መነጋገሪያ ርዕሶችም ይዟል ብለን እናምናለን። ከራሳቸው ከደጃዝማች አያሌው ብሩ ጀምሮ እስከ ንጉሡና በእሳቸው ስር ለነበሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሚና አንድ ነገር ሲሆን፤ በየክልሉ ገበሬውና ሌላው ተራ ሰው ያደረጋቸው ነገሮች ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። ከጀግንነቱ ጋር ከህደቱ ድንቁርናውም ሆነ የዋህነቱ አብሮ ተገልጧል።

ሌላው አንባቢን የምናሳሰበው ነገር ቢኖር ባለፈ ታሪክ ዳኝነት መስጠት ተገቢ ባይሆንም አስተያዬትና ትችት ግን የማይቀር ነገር ነው። ሰለዚህ አንብበው እስኪጨርሱ ድረስ በተለይ አንድን ወገን ከሌላው ለይቶ ለመተቸት እንዳይቻኮሉ ነው። ደጉና ከፉው በየቦታው ነው የታየው።

እሰጀምሮ ላሰጨረሰን አምላክ ምሰጋና ይግባው

ገበየሁ ተፈሪ
ደሰእለኝ አለሙ




1. የሰሜን ጦር ግንባር አሰላለፍ ካርታ ፀሀፊው የሸፈኗቸውን ቦታዎችና የጉዞ አቅጣጫ መረዳትም ያስችላል፡፡



# ምዕራፍ አንድ

## የታላቅ ሰው ህመም

ጥቅምት 20 እኤአ 1935(በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1928 ዓ.ም) ጥሩ የእሁድ ከሰአት ቀን ነበር፡፡ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መሀከል የሚደረገው ጦርነት ሁኔታ አየገፋ ነው ቢሆንም ለኛ ብዙም ስሜት ሳይሰጠን በአዲስ አበባ በዶክተር ሀነር የሚያምር ቅጥር ግቢ በሥስነስርአት በተዘጋጀ የቡና ጠረጴዛ ዙሪያ ከበን ቁጭ ብለናል፡፡ መንግስተ ሰማያት ከመሰለው ሰማያዊው ሰማይ የአፍሪካ ፀሀይ ታንፀባርቃለች፡፡ ግቢው የተለያየ ቀለም ባላቸው በተተከሉ አበባዎች ተውቧል፡፡ የተቀመጥንበት ወንበር ምቾትን ጨምሮ የቀረበው ቡናና ኬክ ጣዕም ነበረው፡፡

ንግግራችን እንደተለመደው ስለ ጦርነቱና ስለሚያስከትለው አስከፊ ውጤት ስለሚፈጠረው ሽብር ነበር፡፡ ሁላችንም የሊግ ኦፍ ኔሽንስ[1] በአስቸኳይ መፍትሔ እንደሚያገኝለት ተማምነናል ቢያንስ ተስፋም አድርገን ነበር፡፡ የዋህ ቅን ሀሳቢ ስለሆን እንጂ ስለሚመጣው ትልቅ ነውጥ፣ ስለሚያልፈው ህይወትና ስለሚጠፋው ንብረት፤ እኛን ራሳችን ጨምሮ ስለሚደርስብን መከራ ትንሽም ቢሆን ሀሳቡ አልነበረንም፡፡

ሰው ያሰባል እግዚአብሔር ይፈፅማል፡፡

ድንገት ከበር በኩል ትልቅ ባለሥልጣን ሰው ወደ ግቢው ሲገቡ አየን፡፡ የአቢሲኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብላቴን ጌታ ህሩይ ናቸው፡፡ ፊታቸው የህፃን ልጅ አይነት ከብነት ያለው ሲሆን ፀጉራቸው ነጭና ሎጫ ነው ከእግራቸው በኩል ወደ ደጋንነቱ ያጋድላል፡፡ ወዲያው እንዳየሁዋቸው እኔን ፈልገው እንደመጡ ገመትኩ፡፡

ትክክል ነበርኩ፡፡ ትንሽ አረፍ ብለው ቡና ከጠጡ በኋላ ስለመጡበት ጉዳይ መግለፅ ጀመሩ፡፡ መልክታቸው ከንጉሡ የመጣ ነው፤ የተጠየቅሁትም በሚቀጥለው ቀን ወደ ስሜን ግዛት ዋና ከተማ ወደ ዳባት በአውሮፕላን

1 (League of Nations) በዚያን ጊዜ የነበረው የአለም መንግሥታት ማህበር

መሄድ የምችል እንደሆን ነው፡፡ ስመ ጥሩው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ታመዋልና የህክምና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ቶሎ የህክምና እርዳታ ተደርጎላቸው በሰሜን ግንባር ወደ ጦርነት እንዲሄዱ ይፈለጋሉ፡፡ የአቢሲኒያው ንጉሥ  ጃንሆይ (አፄ ኃይለ ሥላሤ) መልስ ስለሚጠብቁ ቶሎ መልስ መስጠት ነበረብኝ፡፡

ወዲያውኑ አወጣሁ አወረድኩ ጥያቄው ከጃንሆይ ስለመጣም መልስ በቶሎ መሰጠት ነበረብኝ፡፡ ነገሩ ጥሩ አጋጣሚና የሚያጓጓ ሆኖ እንዳገኘሁት ማሰቤን መደበቅ አልችልም፡፡ የስድስት መቶ ኪሎሜትር ርቀት ያለውን ቦታ በአውሮፕላን መብረር፤ በአውሮፕላን መብረርም የመጀመሪያዬ ስለሆነ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ያላየሁትን ምዕራባዊ የሰሜኑን የአቢሲንያን ክፍል ማየትም የማይገኝ ጥሩ አጋጣሚ ስለነበረ ነው፡፡ ተጨማሪ ገንዘብ የማግኘት ሁኔታም የሚጠላ አይደለም፡፡ በጎን በኩል ደግሞ የመረበሽ ስሜት ተሰማኝ፡፡ የሄድኩበትን ጉዳይ ከጨረስኩ በኋላ  አስታውሰው ይመልሱኝ ይሆን ወይስ እዛው ጫካ ጥለውኝ ለረዥም ጊዜ እቆይ ይሆን ብዬ አሰብኩ፡፡ እንደዚህ ለማሰብ ደግሞ በቂ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች ነበሩኝ፡፡

መጀመሪያ ለዚህ አይነት አደጋ ላለበት ሥራ የገንዘቡን ጉዳይ ግልፅ አድርጎ  መነጋገር ወይም መጨረስ አለብኝ ብዬ አሰብኩ፡፡ ለዚህም ዕጥፍ እንዲከፈለኝ እና የሕይወት መድህን ወይም ኢንሹራንስ እንዲኖረኝ መጠየቅ ተገቢ ነበር፡፡  ከልምድ በመነሳት ግን ከሀበሾች ጋራ ኮንትራት ሲዋዋሉ ለመከራከሪያ እንዲሆን ዋጋን ከፍ አድርጎ መጥራት የተለመደ በመሆኑ የሚከፈለኝን ሂሳብ በሶስት ዕጥፍ ከፍ ለማድረግ አሰብኩኝ፡፡ ብላቴን ጌታ ከተቀመጡበት ወንበር ትዕግሰት አጥሯቸው በመቁነጥነጥ ጃንሆይ ቁጭ ብለው መልሴን እንደሚጠብቁ አስታወሱኝ፡፡

ዶክተር ህነርን ምክር ጠየቅሁት፡፡ የበረራ ልምድ ስላለው በአውሮፕላን መብረሩ የሚያስደስት አጋጣሚ መሆኑን እርሱ ራሱ ይህንን አጋጣሚ ቢያገኝ የሚቀበለው ሀሳብ ነው፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ ሌላም ሰው መረዳት እንደሚችለው በእንደዚህ አይነቱ የግል ውሳኔ ጉዳይ ምክር መስጠት አልፈለገም፡፡ ስለሆነም ለውጭ ጉዳይ ሚኒሰትሩ ጉዞውን የሚከተሉት ነገሮች ከተሟሉ የምቀበለው ነገር መሆኑን በአግባቡ ገለፅኩላቸው፡፡

መሟላት ያሉባቸው ነገሮች

አንደኛ የምወስዳቸው የሚያስፈልጉኝ መድሃኒቶች እንዲዘጋጁ



ሁለተኛ ደጃዝማች አያሌው እንደተሻላቸው ወድያውኑ የምመለስበት አውሮፕላን እንዲላክልኝ

ሶስተኛ ደግሞ ክፍያዬ በሶስት እጥፍ እንዲሆንና ለቤተሰቦቼም ማስተማመኛ ኢንሹራንስ እንዲሰጣቸው ነው፡፡

ጠቆር ብሎ የነበረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ፊት ፈካ አለ፡፡ ጉዞውን ለማድረግ በመሰማማቴ አመስግነውኝ ከመቀመጫቸው ተነስተው እንደቆሙ ካቀረብኩት ጥያቄዎች ቁጥር አንድና ሁለት እንደሚሟሉ ቃል ገቡልኝ፡፡

ደጃዝማች አያሌውን ያመማቸውን ነገር ማወቅ ፈልጌ ብጠይቅም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ምንም የሚያውቁት ነገር እንዳልሆነ ነው የተገነዘብኩት፡፡ ሚኒስትሩ ከታማሚው ጋራ በስልክ የተገናኙ ቢሆንም መታመማቸውን ብቻ ማወቅ እንጂ ተጨማሪ ነገር የዶክተር ችግር እንጂ የሳቸው አለመሆኑን ነው የተገለፀው፡፡ እንደሚኒሰትሩ አገላለፅ ሀኪም ስለበሽተኛው ሁኔታ አስቀድሞ ማወቅና የሚያስፈልገውን መድሃኒት ማዘጋጀት እንደሚኖርበት አልታያቸውም፡፡ ፋርማሲ ያለው ደግሞ ከዳባት 600 ኪሎሜትር ርቀት በአዲስ አበባ ብቻ ነው፡፡ ይህም በጊዜው በነበሩ የአቢሲኒያ ባለሥልጣኖች በየጊዜው ከሚታዩ እርቆ ከማሰብ ጉድለት ከሚፈጠሩ ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡

ሶስተኛውን ጉዳይ በሚመለከት ግን ሚኒስትሩ ራሳቸው ጃንሆይን አማክረው የሚደረግ ነገር መሆኑን ነገሩኝ፡፡ ለመከራከሪያ እንዲሆን ብዬ ሁሉንም ከፍ አድርጌ ስለጠየቅሁ የሚወሰነው የመጨረሻ ውሳኔ ለኔ የሚጠቅም ትክክለኛ ይሆናል፡፡


በነጋታው የአየር በረራ እንደማይኖርም በደንብ ተረድቻለሁ ምናልባትም ከሳምንት ካለዛም ከወር በኋላ  ሊሆን ይችላል፡፡ ግን አሁን ጊዜው ለወጥ ስላለ ከአንድ አራት ቀን በኋላ  ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ፡፡ እንዳልኩትም ሊሆን ነው፡፡ ለጉዞው ራሴን ሳዘጋጅ በዚህ በሰሜን ክፍል ለትንሽ ቀናት እንደምቆይ አድርጌ ነው፡፡ ከመንግስት ጋር የተዋዋልኩበትን ይህን ሥራ እንዳከናውን የሚያስፈልጉኝን የህክምና መሳሪያዎችና የመድሃኒቶችን ዝርዝር ሰጠሁ፡፡

የደጃዝማች አያሌው ህምም እንደተሰማ በጊዜው በአዲስ አበባ በነበሩት መቶ አምስት የውጭ ጋዜጠኞች ያለ የሌለ ወሬ ይዛመት ጀመር፡፡ እኔ ራሴም ስለ ህመማቸው የማውቀው ጉዳይ የለም ብዬ መግለጫ ብሰጥም ደግሞ ደጋግሞ ቃለ መጠየቅ ከማድረግ አላደነኝም፡፡ ጋዜጠኞቹ ለየጋዜጣቸው

በተረጋጋ ሁኔታ ስለ ደጃዝማች እያሌው ቴሌ ግራም ያደርጋሉ:: በቴሌ ግራማቸው ደጃዝማች እያሌው ከኢጣልያ ጋራ በተደረገው በመጀመሪያው ጦርነት በጣም ስለቆሰሉ ዶክተር በአውሮፕላን ሊላክላቸው ነው የሚል ነበር::

እንደእውነቱ ከሆነ ደጃዝማች እያሌው ከጦርነቱ ግንባር ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ነው ያሉት:: እንዲህ አይነቱ ያልተረጋጋጠ ውሸት ወይም ወሬ ሲወራ ማንም ሰው ሊረዳው እንደሚችለው ሃበሾችን ማናደዱ አይቀርም:: ሁለት ጊዜ በጦር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተጠርቼ ምን ብዬ እንደተናገርኩ ተጠየቅሁ:: በሁለቱም ጥያቄ ጊዜ አስቸጋሪ ይሁን እንጂ በኔ በኩል እንደዚህ አይነት ሃሜታ እንዳልተናገርኩ በመንገር አረጋግቻለሁ:: ያም ሆኖ ሰላዮች እየተላኩ የማደርገውንና የምናገረውን ነገር ይከታተሉ ነበር ከዚያም አልፎ የግል ሠራተኞቼ በሚሥጥር ይጠየቁ ነበር::

ስለጉዞው ሁኔታ የሚገልፅ ምንም አይነት ዜና ሳይኖር ቀናቶች አለፉ:: እኔም እንግዲህ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ጉዞው ተሠርዟል ማለት ነው:: እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለሁም ብዬ ማሰብ ጀመርኩ:: ለሰባት አመታት በታማኝነት በአገለገልኩት መንግስት አልታመንም ማለት ነው የሚለው ሀሳብ ሲሰማኝ ደግሞ ያስጨንቀኝ ጀመር:: በዚህ ምክንያትም ጥቅምት ሀያ ሶስት ቀን ከሰአት በኋላ በጓደኞቼ በተደረገለኝ ግብዣ ስመገኘት ወደ ኢምፒሪያል ሆቴል ሳመራ ደስተኛ አልነበርኩም::


የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጉዳይና ፡ በጦርነቱም ፡ ዘመቻ ፡ ምክንያት ፡ ኦፊሲዩል ፡ ያልሆነ ፡ የፖለቲካ ፡ ነገር ፡ ማውራትና ፡ መነጋገር ፡ በፍጹም ፡ ተከልክሏል ።

(፩) ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎ ፡ የፖለቲካ ፡ ነገር ፡ ሲያወራ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ እየታየ ፡ ከ፶ ብር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይቀጣል ፡ ወይም ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ደንብ ፡ ይፈጸምበታል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር ፡ ሲያወራ ፡ የተገኘውን ፡ ሰው ፡ በግልጽ ፡ ከሶ ፡ ወይም ፡ በስውር ፡ ለባለሥልጣን ፡ እስታውቆ ፡ ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ ለሚያስረዳ ፡ ሰው ፡ ከመቀጫው ፡ ገንዘብ ፡ እኩሌታው ፡ ይፈቀድለታል ።

መጋቢት ፡ [illegible] ቀን ፡ [illegible] ፡ ዓ ፡ ም ።

P 2

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከንቲባ ።

በወቅቱ ጦርነቱን አስመልክቶ በመንግሥት ከወጡ ማስታወቂያዎች አንዱ



መንገድ ላይ እያለሁ የቆንስላችን መኪና ድንገት ደረሰብኝ:: ሾፌሩ በየቦታው እየተፈልግሁ እንደሆነና በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል ሄጄ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ማግኘት እንዳለብኝ ነገረኝ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከብላቴን ጌታ ህሩይ ፊት ቆጭ አልኩ:: ሁሉም ነገር ስለተዘጋጀ በነጋታው መብረር እንዳለብኝ ተነገረኝ:: መድሃኒቶች አውሮፕላኑ ወስጥ ተጭነዋል የቀረ ነገር ቢኖር ውሉን መፈራረም ብቻ ነው::

ወረቀት እውጥተው ንጉሡ እየጠበቁ ስለሆነ በአስቸኳይ እንድጨርስ ትዕዛዝ ሰጡኝ:: የችኮላው ምክንያት ገብቶኛል:: ነገር ግን የውሉን ፅሁፍ በጥርጣሬ ተመለከትኩ:: ሁሉም ነገር እንደጠየቅሁት የተፃፈ ሲሆን ያው የገንዘብ ከፍያው ጉዳይ ግን እንደጠየቅሁት አይደለም:: ለመከራከር እንዳይመችም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስም ያለበት ማህተም አርፎበታል::

እኔም ራሴ ቢሆን ተጨማሪ ወይይት ወይም ክርክር ለማድረግ አልተዘጋጀሁም:: ወዲያውኑ ፊርማዬን ሰጥቼ ወደ ሆቴሉ አመራሁ:: በሆቴሉም የክብር እንግዳ እንደመሆኔ በተዘጋጀው የመስነባበቻ ግብዣ ላይ ተገኝቼ ተቀመጥኩ:: የታወቀ የሲኒማ ካምፓኒ ዳይሬክተርና የኖርዌይ ተወላጅ የሆነችው ባለቤቱ እኔን ለማስደሰት ያዘጋጁት ያማረ ግብዣ ነበር:: ስለተደሰትኩም የነበረኝ መጥፎ ስሜት ሁሉ ለቀቀኝ:: ይህ የአዲስ አበባ የመጨረሻ ምሽት ቢሆንም ለወደፊት ለረዥም ጊዜ ለሚመጣውና ለሚሆነው ነገር ሁሉ በዚህ ደስ በሚል ሁኔታ ተጀመረ::



በአዲስ አበባ የደጃዝማች እያሌው መኖርያ ቤት(በፋሲል ጊዮርጊስ መልካም ፈቃድ )from the book: The City & Its Architectural Heritage by Fasil Ghiorgis and Denies Gerard

# ምዕራፍ ሁለት

## ወደ ሰሜን

ከጠዋቱ አስር ሰአት ተኩል ሲሆን ተነሳሁ ሻንጣዬን ከሞላሁ በኋላ በተጨማሪ ታጣፊ አልጋና የመኝታ ከረጢት ወይም (ስሊፒንግ ባግ) ያዝኩ፡፡ ይህንን ብቻ ነው ለመውሰድ የወሰንኩት፡፡ አንድ ስኒ ቡና ከጠጣሁ በኋላ ለሠራተኞቼ የቤት እቃዎቼን ፈረሶቼን ሌሎችንም ነገሮች ጨምሮ እንዲጠብቁ ትዕዛዝ ሰጠሁ፡፡ በሃሳቤ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደምመለስ ነው፡፡ ነገር ግን ትንሽም ቢሆን ያላወቅሁት ነገር እነዚህን በቤቴ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡና ብዙ የቤተሰብ ትዝታ የሚያስታውሱኝን ንብረቶቼን ተመልሼ እንደማላያቸው ነው፡፡ እንዲያውም ቶሎ እንደምመለስ እርግጠኛ ስለነበርኩ ንብረቴን በጥሩና በማያሰጋ ቦታ ለማስቀመጥ ሙከራም አላደረግሁም፡፡

ነገር ግን ንብረትን የማያሰጋ ቦታስ ለማስቀመጥ ቦታው የት ነው የሚገኘው? ከተማው ሲበዘበዝ በቦታው የነበሩ ሰዎች እንኳን አይናቸው እያዩ ቤትና ንብረታቸው ወድሟል፡፡ ለማንኛውም ይህ የሌላ ጊዜ ታሪክ ነው፡፡

ሁሉም ከተዘጋጀ በኋላ  መኪና አሰኪመጣልኝ ድረስ አሥራ አምስት ደቂቃዎች ነበሩኝ፡፡ በዚህ ቆይታ አእምሮዬ ስለጉዞው በሀሳብ ይራወጥ ጀመር፡፡

የመጀመሪያ አውሮፕላን በረራዬ እንዴት ይሆን? ምንያህል ጊዜ ይወስድስ ይሆን? ጠቅላላ ሁኔታውስ ምን ይሆን? ድንገት የአየር በረራውን ካልቻልኩት ብዬ ደርዘን የሚሆኑ የወረቀት ከረጢቶችም ይዣለሁ፡፡

አደጋስ ይደርስብን ይሆን? ወይም ደግሞ የኢጣልያ አውሮፕላኖች አግኝተው ተኩሰው ቢጥሉንስ? እያልኩ መኪና መጥቶ አውሮፕላን ማረፊያው እስኪወስደኝ ድረስ በአእምሮዬ ምስል እየፈጠርኩ ስተራመስ ነበር፡፡ አውሮፕላን ማረፊያው ቦታ እንደደረስንም የሚያንፀባርቅ አልሙንየም ሽፋን ያለው ጃንከር አውሮፕላን ሞተር ድምፁን እያሰማ መንደርደሪያው ላይ



ቆሟል፡፡ ሌላም ተጨማሪ እድሜው የገፋ የፈረንሳይ ፖቴዝ አውሮፕላን ቆሟል፡፡

ለኔ መሆኑን ተረዳሁና ወደ ጃንከሩ ፓይለት ዌበር ይባላል ሄጄ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ እሱም "አየሩ ጥሩ ነው አውሮፕላኔም በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው" ብሎ ነገረኝ፡፡ አጅቦን የሚሄደው ፖቴዝ አውሮፕላን ጉዳይ ግን ሌላ ነው፡፡ መነሳት አልቻለም፡፡  አምስት ሰዎች ተረባርበውበት ከግማሽ ሰአት በኋላ ተነሳ፡፡

ሁለቱም አውሮፕላኖች ከሚጠበቀው በላይ ጭነት ተጭነዋል፡፡ እኔ ያለሁበት አውሮፕላን እኔን ፓይለቱንና መካኒኩን ጨምሮ አራት የህክምና መሳሪያና መድሃኒቶች የያዙ ሳጥኖች፤ አራት አውቶማቲክ መሳሪያዎች (መትረየስ) እና ስድስት ሺህ ጥይቶች ይዟል፡፡ ሌላኛው አውሮፕላን ደግሞ ፓይለቱንና *ድሬሰሩን አራት መትረየስ ከስድስት ሺ ጥይቶች ጋር ሲይዝ በተጨማሪ የመቀስቀሻ ወረቀቶች ጭኗል፡፡ የሚበተኑ መቀስቀሻ ወረቀቶች በአማርኛ ስለ ጦርነቱ፤ ስለ አየር ቦምብና ጋዝ፤ ስለታንክ ምንነትና ሌሎችንም ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ሁኔታ የሚገልፅ ፅሁፍ ነው ያሰባቸው፡፡

ሁላችንም ቦታ ቦታችን ከያዝን በኋላ  አውሮፕላኖቹ እንዲበሩ ምልከት ተሠጠ፡፡ በሜዳው የነበሩ ጓደኞች በመሰናበት እጃቸውን አወዛወዙ ከነሱም መሀል ሆስፒታል አብውረኝ የሚሰሩ ሁለት ስዊድናውያን ነርሶች ነበሩበት፡፡ የኛ አውሮፕላን ከተነሳ በኋላ  ቀርፋፋው ፖቴዝ እስኪነሳ ድረስ በሜዳው ዙርያ እያንዣበብን ቆየን ከትንሽ ጊዜ በኋላ  ፖቴዙም ተነሳና ሁላችንም ወደ ሰሜን አቅጣጫ መብረር ጀመርን፡፡

አጃቢያችን ፖቴዝ አውሮፕላን ፈጣን መሆኑን በማሳየት የ3500 ሜትሮች ከፍታ እየወጣን እያለ መንገዱን ለማሳየትም ሆነ ከኢጣልያ አውሮፕላኖች ለመከላከል ከኛ ቀደም ብሎ መብረር ጀመረ፡፡ የእንጦጦን ጋራ ወድያውኑ ወደኋላችን ትተን የሱሉልታ ሰፊና ለም ቦታ ከሥራችንና ከፊት ለፊት መታየት ጀመረ፡፡ ወርቃማ በመሰሉ የሰብል እርሻዎችና አረንጓዴ ሜዳዎች በጥዋቱ ፀሐይ ብርሃን ምክንያት ብርማ ቀለም የሚያሳዩ ወራጅ ውሀዎች በመሃላቸው ሲፈሱ ይታያል፡፡

ከሩቁ በምሥራቅ በኩል የወታደር ካምፕ ይታያል ይህም የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ነው፡፡ ለሰባት አመታት የዚህ ጦር ሀኪም ነበርኩ፡፡ ወታደሮቹ ከአንድ ቀን በፊት ከአዲስ አበባ ወጥተው ወደ ደሴ እያመሩ ነው፡፡ ወደ ዳባት እንድሄድ ባልታዘዝ ከዚህ ጦር ጋራ ወደ ደሴ  አብሬ እሄድ ነበር፡፡ ሆኖም

*በአሁኑ ጊዜ የጤና ረዳት ተብለው የሚጠሩ የጤና ባለሙያተኞች

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ያው ደሴ እንገናኛለን ብዬም አሰብኩ፡፡ የኔ ሃሳብ ነበር፡፡


የጋዝ መርዝ መከላከያ ። (፳፩)

ለገሙ መቶ ጥይት ከሉብር ከ፪ እስከ ፰ ሳንቲ ሜትር ይታሰባል። ደግሞም ለጋዙ ኃይል የሆነ እንደሆነ ማብዛት ያስፈልጋል ።

ጥቅሙ ፤ ሥራው ቀላል ነው ። የነፋሱንም አካሄድ መመርመር አያስፈልግም ።

ጉዳቱ ፤ በዋጋው ትልቅ ኪሳራ ጋዙ ሳይሠራ ይቀራል ነገር ግን ተመርምሮ መታደሉ አይቀርም ።

ዓይነቱ እንደሚታወቀው ፤ በየማኅሩና በየቅጠሉ ላይ ነጭ ምልክት ይታያል ፤ ደግሞ ጋዙን ሳይተኩሱ በፊት የነፋሱን አካሄድ ለማወቅ የጭስ ጥይት ይተኩሳሉ ፤ በአይሮፕላን ጋዝ መርዝ በምድ ለመጣል የሆነ እንደሆነ በጣም ወደ ላይ ወጥቶ ነው ። እንዲዘንብ ለማርከፍከፍ የሆነ እንደሆነ ግን አይሮፕላኑ በጣም ዝቅ ብሎ ወርዶ ነው ። (፫ኛ ሥዕል ተመልከት።)




P4

፫ኛ ፤ ሥዕል ።

በወቅቱ በመንግሥት የተዘጋጁ ስለ መርዝ ጋዝ ምክር የወጡ ፅሁፎች



የጋዝ መርዝ መከላከያ። (፳፩)




፬ኛ ፤ ሥዕል ።

P 5

በማስክ ላይ የሚገኘው ።

፩ኛ ፤ የማያስገባ ወደ ማጣሪያ ትንፋሽ ስታ ነፋስ የማያስገባ የአፍ ቀለበት ይባላል ።

፪ኛ ፤ ለዓይን መንጥር በሙጭ በኩል በሌሉን ወይም ትሬምስክስ መስተዋት ( የማይሰበር ዓይነት መስተዋት )

ሙሶ የተባለውን የአንድ ጡረታ የወጣ የእንግሊዝ ጄኔራል እርሻን ቁልቁል እየተመለከትኩ እያለሁ ድንገት መሬቱ ከአይኔ መሰወር ጀመረ፡፡ ቀጥ ያለ ተራራ የነበረው እይታ ወደ ታች ጨለማ ወደመሰለ ጎድጓዳ መሰመጥ ጀመረ፡፡ ከዚያም ወንዝ ማየት ጀመርኩ፡፡ አሁን ያለንበት ቦታ ከሙገር ሸለቆና ከሙገር ወንዝ ወለል ወደ ስምንት መቶ ሜትር የሚሆን ከፍ ብለን ነው፡፡ ከዚህ ስፍራ ነው ለአዲስ አበባ ከተማ የሚያስፈልገው ሲሚንቶ የሚመጣው፡፡ በተቃራኒው በኩል ተራራው እንደግድግዳ ቀጥ ብሎ ካለንበት ከፍታ ጋራ ተስተካክሎ ይታያል፡፡

ከፊት ለፊታችን ደግሞ ሌላ ሜዳማ ቦታ ተንጣሎ ይታያል፡፡ የራስ ካሳ ውርስ ስላሴ ነው፡፡ ጥሩና ንቁ ፈረሶች በማርባት በአቢሲኒያ ስም ጥር የሆነ ቦታ ነው፡፡ በቀኝ በኩል ሲመለከቱ ደግሞ የአፄ ሚኒሊክ አልጋ ወራሽ የነበሩት ልጅ እያሱ ይኖሩበት የነበረው የፍቼ ከተማ ይታያል፡፡ ልጅ እያሱ

ለአስር አመት በዚህ ከተማ የተቀመጡ ሲሆን ለማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ ተይዘው ጥብቅ ቁጥጥር ባለበት እስር ቤት ወደ ሐረር ተወሰደዋል::

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን አባይ ወንዝ ደረስን:: ፓይለቱ እኔ እንዳይ የፈለገው አስደናቂ እይታ አዘጋጅቶልኛል:: በአይን ሲያዩት ግርማ ሞገስ ያለው አይታም ነበር:: ከጊዜ ብዛት የአባይ ወንዝ ወደ ታች በመሸርሸር 1500 ሜትር ጥልቀት ያለው ሸለቆ ፈጥሯል:: ፀሃይ ወደ ላይ ገና ከፍ ስላላለች ታችኛው የሸለቆ ክፍል በደንብ ባይታይም ወንዙ ከስር የአለት ንጣፍ ላይ ሲወርድ ይታያል:: የሸለቆው ግድግዳ ወደ ሰላሌ በኩል በዛፍና በዕፅዋት የታጀበ ሲሆን ወደ ጎጃም በኩል ግን ግራጫ መልክ ያለው ቋጥኝ ነው የሚታይበት::

ከሸለቆው ወጥተን እየበረርን ያለንበት የጎጃም ክፍል በአረንጓዴ ሜዳዎች ጫካና ከተሞች የተሞላ ነው:: ሰዎች ሠፍረውበታል:: ለአይን የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ የቤተክርስቲያኖች ብዛት ነው:: በዚህ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች ፅኑ አጥባቂ ሀይማኖተኞች ናቸው ተብለው በአቢሲኒያ ይታወቃሉ::

ወደ ግራ በኩል ደግሞ የጎጃም ትልቁ ተራራ ጮቄ ይታያል:: አናቱ በ4150 ሜትር ከፍታ ላይ በደመና ተሸፍኗል:: ከአባይ ማዶ ወደ ቀኝ በኩል ደግሞ የአማራ ሳይንት ተራራማው መሬትና የ4350 ሜትር ከፍታ ግርማ ሞገስ ያለው ሊጋምቦ ተራራ ይታያል::

ከግማሽ ሰአት በረራ በኋላ ጥቁር አባይን እንደገና አቋረጥን:: ወንዙ ከጣና ሀይቅ ተጠምዞ ሲወጣ በደንብ ማየት ይቻላል:: አባይ ጎጃምን በሶስት ጎን አካሎ ነው የሚወርደው:: ከዚህ ከጥምዙ ቦታ በመነሳት ወደ ዳባት ቀጥታ መስመር ያዝን:: ሸለቆው እዚህ አካባቢ ጥልቅ ስላልሆነ ወንዙ በድንጋይ በተሠራ ድልድይ ሥር ሲወርድ ተመለከትን:: ድልድዩ የተሠራው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ፋሲል ነው:: የድልድዩ ሥራ ከሚከተለው ታሪክ ጋራ የተያያዘ ነው::

አፄ ፋሲል ባለፀጋና ገናና ንጉሥ ነበሩ:: በሕይወታቸው ዘመን ብዙ የከፋ ነገር ያደረጉም ያሳለፉም ነበሩ ይባላል፤ ወደኋላ በእርጅና ግን ፀፀት ስለገባቸው ንስሐ መግባት ፈለጉ:: ማቅ ለብሰው አናታቸው ላይ አመድ ነስንሰው በባዶ እግራቸው ወደ የሚያውቁት ባህታዊ ሄደው ለነብሳቸው ሰላም ለማግኘት ምን ቢያደረጉ እንደሚበጅ ጠየቁ:: ባህታዊ ሲመክራቸው በዝናብ ወራት ወንዝ በማቋረጥ የሚሞተው የህገሬው ህዝብ በሺ የሚቆጠር ስለሆነ ወንዞች ላይ ድልድይ ብትሰራ ይሻለል ብሎ መከራቸው:: አፄ



ፋሲልም በሀሳቡ በመስማማት ድልድይ እንዲሰራ ትዕዛዝ ሠጡ:: በተጨማሪም ድልድዩን የሚያቋርጥ ሰው በሙሉ ለንጉሡ ለአፄ ፋሲል ፀሎት እንዲያደርግ ትዕዛዝ ሠጡ:: ይህ ፀሎትም እስካሁን ድረስ የሚደረግ ነው:: በድልድዩ የሚያልፈው መንገደኛ እግዚአብሄር የአፄ ፋሲልን ነብስ ይማር በማለት ይፀልያል::

አሁን ደግሞ የበጌምድርን ክፍል እያቋረጥን ነው:: አገሩ በተራሮችና ፀሃያማ በሆኑ ረባዳ ስፍራዎች የተሞላ ነው:: የበግ እርባታ በጣም የዳበረበት ሲሆን የአቢሲኒያ ምርጥ የአህያ ዝርያዎች የሚረቡበት ቦታ ነው:: ነዋሪዎችም በጣም ሀይማኖተኞች ናቸው:: ታወቂ የሆኑ ብዙ ገዳማት አሉት በሥራችን አምባ ማርያም የተባለውን ትልቅ ገዳም ተመለከትን::

ወዲያውኑ የደብረ ታቦር ከተማን አቋርጠን እየበረርን አለፍን:: ይህ የራስ ካሳ ግዛት ነው:: በከተማው ትልቅ የመኖርያ ግቢ አሰርተዋል:: ትንሽ ፈንጠር ብሎ ደግሞ በከተማው በምሥራቅ ጠርዝ በኩል የአድቬንቲስት ሚሲዮን ማዕከል ከመኖርያ ቤቶች ትምህርት ቤትና ሆስፒታሉ ጋር ይታያል::

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ተኩል ሲሆን በርቀት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የጣና ሀይቅ ታየኝ:: ይህንን ሀይቅ ለማየት የረዥም ጊዜ ምኞቴ ነበር:: በርቀት ስለሆነ በደንብ በዝርዝር ማየት አይቻልም:: ሀይቁ በሰሜንና በምሥራቅ በኩል የማይሎች ስፋትና ርቀት ባላቸው በደንቢያና ፎገራ አረንጓዴ ሜዳዎች ተከቧል:: ደንቢያና ፎገራ በቀንድ ከብት ግጦሽ የሚታወቁ ቦታዎች ናቸው:: በትንሽ ርቀት ፍርሥራሹ የቀረ ይፋግ የሚባል የጥንት ከተማ አየን::

በጎንደር ዘመነ መንግስት ጊዜ ከአምስት መቶ አመታት በፊት መሆኑ ነው ይፋግ ትልቅ የንግድ መነሀሪያ ከተማ እንደነበር ይታወቃል::

ጉዟችንም በበለሳ በኩል አድርጎ እየቀጠለ ነው:: ለአንግዳ የማይመች አደገኛ ቦታ ነው:: በተራሮችና በገደሎች የተሞላ ስለሆነ በድንገት እንኳን አውሮፕላን ለማሳረፍ የሚሆን ቦታ አይደለም:: በዚህ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች እንደተራራውና እንደገደሉ ሁሉ የማይመቹ እንደሆኑ ይነገራል:: አገሩ ለአርሻ ስለማይመች በማጭበርበርና በሽፍትነት የሚተዳደሩ ሰዎች ይበዙበታል፤ ሆኖም ከበለሳ የሚጎረጎረው ማር ግን ባለው መአዛ ታዋቂ ስለሆነ ተፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው::

ልክ ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን መድረሻችን ቦታ ዳባት ደረስን:: የአውሮፕላን ማረፊያው እርጥበት ስለነበረው ፓይለቱ ዌበር ደፍሮ ከማሳረፉ በፊት ስድስት ጊዜ ሜዳውን መዞር ነበረበት:: እንደምንም እየነጠረና

አየተንገጫገጨ አውሮፕላኑ ከሜዳው መጨረሻ ከአንድ ትልቅ ዛፍ ፊት ሰፊት ትንሽ ሜትሮች ርቀት ቆመ:: ከአውሮፕላኑ ዘልዬ ወረድኩ በመውረዴም ደስተኛ ነበርኩ:: በእግር የሚረገጡት መሬት መገኘቱ ራሱ ጥሩ ነገር ነው::

ፊታውራሪ መርሶ ንጉሳዊ እቀባበል ነው ያደረጉልን:: ፊታውራሪው የደጃዝማች አያሌው ልጅ ናቸው:: አባትየው በማይኖሩበት ጊዜ የጦር አዛዥ አሳቸው ናቸው:: በድንኳን ውስጥ የምግብ ጠረጴዛ ተዘጋጅቶም ሰለነበር ወድያውኑ ለመመገብ ተቀመጥን:: ፓይለቱ ቶሎውኑ ወደ እዲስ አበባ አንዲመለስ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር:: ይህም የሆነው የኢጣልያ የጦር አውሮፕላኖች እንዳያገኙት ነው:: ከሁለት ሰአታት በኋላም ኪፓይለቱ ጋራ ተሰነባበትን::

ብቻዬን መሆኔ እንግዳ ነገር ሆነብኝ:: ከጥቁር ሰዎች መሃከል በመሃል ጥቁር አቢሲኒያ ብቸኛ ነጭ ሰው መሆኔ ነው::



# ምዕራፍ ሶስት

## ጉዞ በአጃቢ መቀጠል

ከእዲሰ አበባ ከመነሳቴ በፊት ፊታውራሪ መርሶ ከአዲስ አበባ በቴሌፎን ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጥቷቸዋል:: ትዕዛዙም አጃቢ አዘጋጅተው እንዲጠብቁና እኔ እንደደረስኩ ወድያውኑ ደጃዝማች አያሌው ወዳሉበት ካምፕ ወደ ጠገዴ እንድሄድ ነው:: ጠገዴ ከዳባት ወደ ሰሜን በኩል የሶስት ቀን መንገድ ይርቃል::

መንገድ ለመጀመር ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ እንደሆነ ብዬ እኔው ራሴ ስጠይቅ ፊታውራሪ ሁሉም ነገር ለነገ ይዘጋጃል የሚል መልስ ሠጡኝ:: ጠጅ አየጠጣን ወሬ ቀጠልን፡ ከዚያም ከአድካሚ ቀን በኋላ ማረፍ ነበረብን:: ፊታውራሪ እውሮፕላኑን ሲጠብቁ ቆመው ስለዋሉ የደከማቸው መሆኑን ነገሩኝ::

እኔም በጣም ተናደድኩና ቤተሰቡን ጨምሬ አስጠርቼ ወረድኩባቸው:: የንዴት ቃሌን ሳወርድ ፊታውራሪ በፅሞና ምንም ሳይናገሩ ቆመው ተመለከቱኝ:: ያሰኝን ተናግሬ ስጨርስ አንዲህ የሚል ቃል ተናገሩኝ “እኔን የገረመኝ ከኛ በተሻሰ የኛን ቋንቋ እየተናገርክ አንጀራውንም ውሀውንም አብረሀ አየበላሀ እየጠጣሀ እንደራሳችን አድርገን የምናይሀ ሰው እንደ ፈረንጅነትሀ ፀባይሀን ማሳመር ነበረብሀ:: ከንጉሡ የተላከ ትልቅ ዶክተር ነሀ ስለዚሀ ራስሀን ማከበድ አንጂ ማቅለል የለብሀም::”

ምን ማለት አችላሰሁ በአነጋገራቸው ያሰምንም መከላከያ ነው የተረታሁት:: ዞሪያውን ልይ ብዬ ጥያቸው ወጣ አልኩ::

የዳባት ከተማ ሌሎች መሰል ከተሞችን ነው የሚመስለው ፤ ወደ ሶስት ሺሀ የሚሆኑ ነዋሪዎች አሉበት:: ከፊት ሰፊታቸው ትንሽ ግቢ ቢጤ ያሳቸው ከብ የሣር ጎጆ ቤቶች በተዘበራረቀ አቀማመጥ ከጋራው ስር ተዘርግተዋል:: ጠበብ ያሉ የተጠማዘዙ የአግር መንገዶች በተሰያዩ አቅጣጫ አርስ በራስ አያቋረጡ በመንደሮች ውስጥ ይታያሉ:: ከላይ ከከፍታው የቅዱስ ገብርኤል

ቤተከርሰቲያን በወይራና በጥድ ዛፎች ታጅቦ ከፍ ባለ አጥር ዙሪያውን ተከቦ ይታያል፡፡ እያንዳንዱ ሱቅ ሻጭ ንግዱን በየትንንሽ ቤቱ ውስጥ ስለሚያደርግ ከፍት ሱቅ የሚባል ነገር አይታይም፡፡ ከከተማው ወጣ ብሎ ወደ ግቢ ወይም ወደ ቤተ መንግስቱ መሄጃ በኩል ቅዳሜ ቅዳሜ የሚውል የገበያ ቦታ ይታያል፡፡

ቤተመንግስቱ ለመድረስ አንድ ሰው ከባህር ወለል ሶስት ሺ ሜትር ከፍታ ወደ ላይ መውጣት አለበት፡፡ ቤተመንግስቱ ራሱ አንድ ሺ ሜትር ርዝመት ካለው ገደል ተጠግቶ ነው የተሠራው፡፡ ከዚያ ሆነው ዙሪያውን ሲመለከቱ አስገራሚ ነው፡፡ ስለ ሰሜን ተራሮችና ገደሎች ብዙ ሰምቻለሁ ነገር ግን በአይን ሲታይ እንደሚሆነው አይደለም፡፡ የተራሮቹ አናቶች ጠፍጠፍ ያሉ ሆነው አንደ ሺ ሜትር ወይም ከዛ በላይ ቁመት ባለቸው ገደሎች ይከፋፈላሉ፡፡ የተዘበራረቀ ግን እስገራሚ የሆነ አይታ አላቸው፡፡ ያለው ንፁህና ድንግል የተፈጥሮ ውበት ሰውነቴን ወረር አስከሚያደርገኝ ድረስ በአድናቆት ተመለከትኩ፡፡

ወደ ግራ በኩል በግምት ወደ መቶ ኪሎሜትር ርቀት በፀሀይ ግባቱ ምክንያት ጠቆር ብሎ 3500 ሜትር ከፍታ ያለው የሚያስፈራው የጠገዴ ተራራ ሰንሰለት ይገኛል፡፡ ወደዚያ ነው የምሄደው፤ አሁን ግን ስለመንገዱ ማሰብ አልፈለግሁም፡፡

ከፊት ለፊት ሲመለከቱ ዝቅ ብሎ ቆላ ወገራ ይገኛል፡፡ የጀበና ቅርፅ ነው ያለው፡፡ አንዳው ትንሽም ቢሆን ሜዳማ ቦታ ማግኘት ይከብዳል፡፡ አገሩ የተሞላው በተራሮች አናትና ጥልቀት ባላቸው ጠባብ ገደሎች ነው፡፡ በቀኝ በኩል በምትጠልቀው ፀሀይ የመጨረሻ ጮራ ፍንጣቂ ብርሃን ሲመለከቱ የትልቁ የስሜን ተራራ ጉብታዎች በበረዶ ተሸፍነው ይታያሉ፡፡

ሁሉም ነገር የሚያስደንቅ ታላቅ ግርማ ሞገስ አለው፡፡ በተፈጥሮ ታላቅነት ምክንያት የትንሽነት ስሜት ተሰማኝ፡፡

በመገረም የራሴን ስሜት ዝቅ አድርጌ ወደ ቤተመንግስቱ አመራሁ፡፡ ትንሽ የምታምር ከፍል ተዘጋጅቶልኛል፡፡ ወለሉ ላይ የፋርስ ሲጋጃዎች ተዘርግተዋል፡፡ የብረት አልጋው አዲስ አንሶላዎች ተነጥፈውበታል፡፡ ወደ ከፍሉ ስገባ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ የነሳ የልጅ አገልጋይ በሁለት እጆቹ ሻማዎች ይዞ በአንዱ ማዕዘን በኩል ቆሚል፡፡ ተከትለውም የእጅ መታጠቢያ ውሃ፤ ምግብ፤ ጠላና ጠጅ የያዙ አገልጋዮች በሰልፍ መግባት ጀመሩ፡፡

ጣፍጦ የተሠራው ወጥ ሽታ የምግብ ፍላጎቴን ስለጨመረው በደንብ



አድርጌ በላሁኝ፡፡ በልቼ እንደጨረስኩ ፊታውራሪ የአዲስ አበባን ሁኔታ ወሬ ለማዳማጥ መጡ፡፡ እኔ ግን በአውሮፕላን ካደረግነው ረዥም መንገድና ሆዴ እስኪሞላ በበላሁት ምግብ ምክንያት እንቅልፍ እንቅልፍ ስላለኝ ድምፅ እያሰማሁ ማዛጋት ጀምርኩ፡፡ በአቢሲኒያ አንድ ሰው ማረፍ ፈልጎ ድምፅ እያሰማ ቢያዛጋ ነውር የለውም፡፡

ፊታውራሪም "ደህና እደር" ብለው ጥለውኝ ሄዱ፡፡

ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ሲሆን ድንገት ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ በመላው ሰውነቴ ላይ የተጣበቀና የሚለበልብ ስሜት ተሰማኝ፡፡ መብራት አብርቼ አቅርቤ ስመለከት አልጋው በቁንጫ ተወሯል፡፡ ስተኛበት ነጭና ንፁህ የነበረው አንሶላ አሁን በደምና በሞቱ ቁንጫዎች ምክንያት ቀለሙን ቀይሯል፡፡

ተነስቼ ስቆምም ቁንጫዎቹ በእግሬ በኩል ወደ ላይ ወረሩኝ፡፡ አንዳንዶችም ፊቴ ላይ መፈናጠር ጀመሩ፡፡ በኋላ እንደተረዳሁት ቁንጫዎቹ በጣም ተርበዋል ምክንያቱም ለብዙ ሳምንታት አዛች ከፍል ውስጥ ገብቶ ያደረም አልነበረም፤ በተጨማሪ ምንጣፎቹ ከተራገፉ ወራት አልፏቸዋል፡፡

አገልጋዩን ቀሰቀስኩና ከውጭ ድንኳን እንዲወጥርልኝ አደርጌ ከአንድ ሰአት በኋላ እንደገና እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ያሁኑ ግን ያልተቋረጠ ነበር፡፡

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን ፊታውራሪ መጡ፡፡ እንደተሰማኝ ከሆነ ከመጠን በላይ ሞቅ ያለ ሰላምታውና ወዳጅነቱም ትንሽ የተጋነነ መሰለኝ፡፡ በዚህ ምክንያትም አንድ የማይሆን ነገር እንደተፈጠረ ተገነዘብኩ፡፡ ሚስጥሩ ሲወጣ ረዥም ጊዜም አልወሰደም፡፡ ለካስ ለመንገዳችን የምንወስዳቸው አህዮች ሲያስፈልጉ ለነገ ካልሆነ በስተቀር ለዛሬ አልተገኙም፡፡

አሁን ግን እንደ ተራ ፈረንጅ ሳልሆን ድሬሰሩን ጠርቼ ምንም ሳልል ከቤቱ ወጥቼ ቁልቁለቱን መንገድ ያዝኩ፡፡ ፊታውራሪም የሆነ ነገር አለ ብለው በማሰብ ሰውነታቸው የሚፈቅድላቸውን ያህል እየሮጡ ከኋላዬ በመድረስ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ወዴት እንደምሄድ ጠየቁኝ፡፡

እኔም በምን ግዴ አመላለስ የምሄደው ወደ ቴሌግራም ቤት ሲሆን እሰዎ የተሰጠዎትን ትዕዛዝ እንዴት አድርገው እንደፈፀሙ ትዕዛዙን ለሠጡዎት ንጉሥ ለማስተላለፍ ነው አልኩ፡፡

አባባሌ ሥራውን ሠራ፡፡ ፊታውራሪ ወዲያውኑ የሚያስፈልገው ነገር ተዘጋጅቶ ጉዞው በሁለት ሰአታት ውስጥ እንደሚጀመር ቃል ገቡልኝ፡፡

ሁለት ሰአት የተባለው ወደ ስድስት ሰአታት ተራዘመ፤ ነገር ግን ከቀኑ ስምንት ሰአት ሲሆን ጉዞውን መጀመር ተቻለ፡፡ ከተጓዦች መሀል ፈጠነ

የሚባለው የኔ ድሬሰር፤ ሁለት የጦር መኮንኖች፤ አንድ መቶ የታጠቁ ወታደሮች ከነሱም ስምንቱ አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ፤ መድሃኒትና የህክምና ቁሳቁሶች፣ የኔን የግል ዕቃዎችንና ጥይቶችን የጫኑ አስር አህዮች ነበሩበት:: ይህን ያህል አጀብ የግድ አስፈላጊ ነበር፤ ጦርነት ላይ ስለሆን የፀጥታው ጉዳይ አስጊ ነው::

በዳባትና ጠገዴ መሀከል ያለው ርቀት ወፍ የሚበረው ሀምሳ ኪሎሜትር የማይሞላ ሲሆን በመሀከል ግን ሰፊና ጥልቀት ያለው ገደል ስላለ ይህንን ለማቋረጥ መንገዱ በእጥፍ ይረዝማል::

የመጀመሪያ ማረፊያ ካምፓችን ያደረግነው ቁልቁለቱን ጨርሰን ነው:: ወንዙ ድረስ እየተንደረደርን የወረድነው ቁልቁለት ከዳባት ከተማ 1200 ሜትር ዝቅ ብሎ ነው:: ደራ ይባላል:: በአግራችን መውረድ ነበረብን በዚህ ቁልቁለት በክብት ጫንቃ ላይ የሚመችም አይደለም፤ መንገዱም ቢሆን በየመሀሉ በድንጋዮችና በገደል ስንጥቆች ይቋረጥ ነበር::

ከመጠን በላይ ስተጫኑት አህዮችም አዘንኩ:: እንዳይንከባለሉ በፊት ለፊት ሰኮናቸው እየተንፏቀቁ ነው ቁልቁለቱን የሚወርዱት:: የጀርባቸው አጥንት ሲንጫጫ ትንፋሻቸው ሲያቃትት መስማት አሳዛኝ ነገር ነበር:: ደግነቱ እርፈውና ተቀልበው የሰነበቱ ስለሆኑ ጠንካሮች ነበሩ:: ጉዞ ስንጀመር የጫንቃ ወይም የጀርባ ቁስል የነበረው የጭነት ክብት አልነበረም::

እንደዚህ አይነት መንገድ ወጥቶ የሚያውቅ ሰው ቁልቁለትን በፍጥነት ለረዥም ሰአታት መውረድ ምን አይነት ሁኔታ እንደሚፈጥር ያውቃል:: ጉልበት ይርዳል ሰውነትም እንዳለ ቁስለት ስሜት ይኖረውና ትልቁም ትንሹም የሰውነት እንቅስቃሴ ህመም ይፈጥራል:: ሰውም ሆነ እንስሶች ሁላችንም ማረፊያው ቦታ ስንደርስ በጣም ቢደክመን አያስገርምም::

የሚያሳዝነው ግን ሁለት አህዮች ከጀርባቸው ላይ የብርቱካን ፍሬ የሚያክል እብጠት ተገኘባቸው:: ሌላ የሚደረግ ነገር አልነበረም:: ሁለት የብረት መተኮሻዎች ለዚሁ ጉዳይ ተብለው ተጭነው ስለሚጓዙ እነሱን በእሳት አግሎ እብጠት ያለውን ክብት አስተኝቶ እብጠቱን በትኩስ ብረት መጥበስ ነው:: አሰቃቂ ቢመስልም ለእንደዚህ አይነቱ ቁስል በጊዜው ፍቱን የሆነ ድርጊት ነው:: እብጠቱን በጋለው ብረት በአግድሞሽ ሰንበር እስኪያወጣ ድረስ በመስመር በመስመር እያደረጉ መጥበስ ነው:: ወዲያውኑ ሲደረግም ውጤቱ የተሻለ ይሆናል:: የጠባሳው ርዝመትና ብዛት እንደእብጠቱ ትልቅነት ነው:: ክብቶቹ ከተጠበሱ ከአንድ ሰአት በኋላ ለጭነት ዝግጁ ይሆናሉ::



ይህ ሁኔታ ህመም የሚፈጥር ቢሆንም የክብቶቹ ጀርባ ተጨማሪ ጉዳት አያሳይም:: ቁስሉ በየቀኑ ለብ ባለ ውሃና በሳሙና ከታጠበና እየተጫኑም ቢሆን በደንብ ከተያዘ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ጨርሶ ይድናል:: የተፈጠረው ጠባሳ ደግሞ ጥንካሬው ይጨምራል፤ ያጋደለ ወይም ያልተስተካከለ ጭነትን የሚችል ሆኖ እብጠት እንደገና እንዳይፈጠር ይረዳል:: እንዲያውም የዚህ አይነት ጠባሳ በጀርባው ላይ ያለው የጋማ ክብት ተፈላጊና ዋጋውም ከፍ ያለ ነው የሚሆነው:: ክብቱም "አልፎታል " ይባላል::

መጨለም ጀምሮ ነበር እኛም ሁለቱን አህዮች አክመን እየጨረስን ነበር:: ድንገት የታጠቁ ወታደሮች ከሰሜን አቅጣጫ ወደኛ ሲመጡ አየን:: ቁም የሚል ጩኸት ሲያሰሙ ሁላችንም መሳሪያችን አቀባበልን:: ደግነቱ ምንም አደጋ አልተፈጠረም:: ወታደሮቹ ደጃዝማች አያሌው እኛን እንዲያጅቡ የላኳቸው ነበሩ:: እነዚህ ስለመጡ መጀመሪያ አጅበውን የመጡት የፈታውራሪ መርሶ ወታደሮች ወደ አለቃቸው እንዲመለሱ ተደረገ::

በጥዋት መንገድ ስለምንጀመር የተጫነውን ሁሉን ነገር አዲስ ለመጡት ወታደሮች ማስረከብ ማታውኑ መደረግ ነበረበት:: እንግዲህ የተፈጠረውን ውዝግብ ማስተዋል ነው:: አቢሲኒያውያን ክርክር የሚወዱ እንዲያውም በክርክር የተካኑ ሰዎች ናቸው:: ከዚህ ቀደም ቁጥር የለሽ ክርክር ሲካሄድ ሰምቼ አውቃለሁ:: የዛሬውን የሚያህል ግን አይቼ አላውቅም::

የመጀመሪያው ውይይት የአህዮችን ቁጥር በሚመለከት ነበር:: ይህ እንኳን የሚያስቸግር አልነበረም:: ጠቅላላ ቁጥራቸው በእጅ ላይ ካሉ ጣቶች ቁጥር አይበልጡም ነበር:: ከአዲሶቹ አጃቢዎች አንደኛው ጠጋ ብሎ ሲመረምር ሁለቱ የተጠበሱ ሆኖ ያያል:: ጠባሳውም አዲስ እንደመሆኑ ሽታው እንኳን አለቀቀም ነበር:: የተነሳው ጥያቄ እንዴት የመጀመሪያ አጃቢዎች ከዳባት ሲነሱ ጤነኛ እንስሳ አልያዙም አሁን እነዚህ የተጎዱ አህዮችን ዋጋስ ማን ሊከፍል ነው ነበር::

አዲስ የመጡት እጃቢዎች ሀላፊነት መውሰድ አልፈለጉም:: በሁለቱ ምትክ ሁለት ጤነኛ አህዮች ይሰጡን ብለው ጥያቄ አቀረቡ:: የዳባት አጃቢዎች ደግሞ የመከላከያ ክርክራቸውን ቁስሉ በግድ የለሽነት የመጣ ሳይሆን በመንገዱ ምክንያትና በተጫኑት የጭነት አይነት ነው:: ይህ ደግሞ አዲስ ነገር አይደለም በየመንገዱ የሚፈጠር ሁኔታ ነው፤ መጠበሱም ቢሆን ጠንካራ ነው የሚያደረጋቸው በማለት አቀረቡ::

ክርክሩ ለአንድ ሰአት ያህል ቀጠለ በኋላ ግን እኔ ራሴ ገባሁበትና በፅሁፍ የሁሉንም ሀላፊነት እኔ እወስዳለሁ ብዬ እቀረብኩ፡፡ ሁለቱን ተከራካሪ ወገኖች የሚስማማ ሀሳብ ስለሆነ በዚህ መንገድ ይኸኛውን ሙግት አስቆምኩት፡፡

ትልቅም ሆነ ትንሽ የአቢሲኒያ ወንዶች በህይወታቸው የሚያስደስታቸው ትልቅ ነገር አለ፡፡ ሁሉም ጠመንጃቸውን መወልወል፤ መፈታታት፤ የተፈታቱትን የመሳሪያ ክፍሎች በፀሀይ ወይም በእሳት ማሞቅ እንደገና መልሶ መገጣጠም ይወዳሉ፡፡ ይህንን ያለማቋረጥ ለሰአታት ግፋ ሲልም ለቀናት ቢያደርጉ ደስ ይላቸዋል፡፡ የእጅ ብረታቸውን በጣም ስለሚወዱ በፍቅር አይን እያዩ ጠመንጃቸውን ይስማሉ፡፡ ይህንን ስለማውቅ አዲስ በመጡት አጃቢዎች ተጭነው የመጡት መሳሪያዎች ይፈቱና ይታዩ ሲባል የመጀመሪያ አጃቢዎች መስማማታቸውን ስሰማ አልገረመኝም፡፡

ሁለት ፋኖሶች እንዲበሩ ተደረገና መሬቱ ላይ ምንጣፍና ሸማ ተዘረጋ፡፡ ከሁለቱም ወገኖች ወታደሮችና ጭፍሮች ዙሪያውን ተቀመጡ፡፡ መሀል ላይ አንደኛው እውቶማቲክ መሳሪያ (መትረየስ) ተቀመጠ፡፡

ቆሜ በትዕግስት የሚደረገውን መመልከት ጀመርኩ፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የእነዚህን ጥንታዊ ተዋጊ ጦረኞችን ጉጉት ለማስታገስ እንደ መስዕዋትነተ ለፍሪዳ ሊቀርቡ ነው፡፡ አሁን እሰራሩን እንኳን በውል የማያውቁትን እንደዚህ የተወሳሰበ መሳሪያ መልሰው ይገጥሙት ይሆን ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እንዴት እንደሚያደርጉ ለማወቅም ጉጉት አደረብኝ፡፡

ለማንኛውም የብሎን መፍቻ እያያዝ ችሎታ አላቸው፡፡ እያንዳንዱን የመትረየስ ክፍል ተራ በተራ ፈቱት፡፡ የተፈታውን ክፍል በደንብ እያዩና እየመረመሩ ሸማው ላይ መቆለል ጀመሩ፡፡ ሁሉም የሚፈታው ነገር ተፈቶ ሲያልቅ የእፎይታ ትንፋሽ በተቀመጡት ዙርያ ተሰማ፡፡ የተቆለለውን ከምር መሳሪያ በሸማ እንደተጠቀለለ እነሱና ሁለተኛውን ያልተፈታውን መትረየስ ይዘው መጡ፡፡ ድንገት ጥርጣሬ ተሰማኝና ለማረጋገጥ ብዬ ሁለተኛውን ከመፍታታችሁ በፊት የመጀመሪያውን መልሳችሁ አትገጥሙም ወይ ብዬ ጠየቅሁ፡፡

የተሠጠኝ መልስ ደግሞ የለም እኛ የምናስበው አንተው መልሰህ እንድትገጥመውና መሥራቱን እንድታረጋግጥልን ነው የሚል ሆነ፡፡

ጥርጣሬዬ ተረጋገጠ፡፡ "በሉ አመሰግናለሁ እንደህፃን ልጆች ከባችሁ ተቀምጣችሁ የማታውቁትን ነገር እንደ አሻንጉሊት ስትበትኑ ያመሻችሁት



ሊሊቱን በሙሉ እኔ እንድገጥመው ልታደርጉኝ ነው ወይ! እናንተ ደደቦች እኔ ሀኪም እንጂ ወታደር መሆኔን አታውቁም ወይ?"

"እሃ! ፈረንጅ ከፈለገ ሁሉንም ማድረግ ይችላል"

"እሱ እንኳን የሚቻል ነገር ነው፡፡ እኔ ግን እንዲህ አይነቱን ነገር መሥራት አልፈልግም፡፡ ይህን አንዱን ብቻ ነው መልሼ ለመግጠም የምሞክረው ሌሎቹን ግን ሳትነኩ እንዳሉ በመጡበት ሁኔታ ማስረከብ አለባችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ማረፍ አለብን፡፡ እኔ የምላችሁን ካልሰማችሁ ግን መሳሪያዎቹን እንደተበተኑ ለደጃዝማች አያሌው ታስረከባላችሁ፡፡ ያ ደግሞ የሚያስከተለውን ነገር ታውቃላችሁ"

ትዕዛዝ የተሞላበት ቃሌ ሥራውን ሠራ፡፡ በህሳቤ ተስማሙ ነገር ግን መከራከር ነበረባቸው፡፡ በአቢሲኒያ መቃወምና መከራከር ባህል ነው፡፡ ይህን የማያደርግ ሰው ከበሬታ ያጣል፡፡

የገባሁትን ቃል ለመፈፀም ቁጭ አልኩና መሳሪያውን እንደገና መግጠም ጀመርኩ፡፡ ያለኝ የሌለኝን እውቀት መጠቀም ነበረብኝ አለበለዚያ የነጭ ስም መጥፋቱ ነው፡፡ እያላበኝና ቁና ቁና እየተነፈስኩ ከብዙ ሙከራና ድካም በኋላ መትረየሱን በነበረበት ሁኔታ መልሼ መግጠም ቻልኩ፡፡

"አሁን ሄደን ማረፍ አለብን" አልኩ

"የለም! አናርፍም"

"አሁን ደግሞ ምን ቀረ?"

"እሃ! ጥይቱ መቆጠር አለበት

ይህስ ትክክል ነው፡፡ ረሰቼ ነው ለነገሩ ጊዜም መውሰድ የለበትም፡፡ በካርታ(መጋዚን) በካርታ የተቀመጠውን መቁጠር ብቻ ይበቃል፡፡ ያገኘሁት መልስ ግን

"የለም እያንዳንዱን ጥይት ነው የምንቆጥረው"

"ምን? ከመጋዚኑ ጥይቶችን ልንፈለቅቅ ነው? የለም እኔ የምላችሁ ይህ በጣም ይበዛል፡፡ እያንዳንዱ ካርታ 750 ጥይት ይይዛል፡፡ አስር ካርታዎች አሉ፡፡ የሚያረካችሁ ከሆነ ሂሳቡን እሰቡና ስንት ጥይቶች እንዳሉ ድረሱበት እኔ ግን ሄጄ እተኛለሁ፡፡"

ለማንኛውም ለጥበቃ ስል ድሬሰሩን መኝታውን የጥይት ሳጥኖች ላይ እንዲያነጥፍ አድርጌዋለሁ፡፡

ከጥዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን መንገድ ጀምረናል:: ወንዙን ሽቅብ ወደ መነሻው እየተከተልን በርቀት መሄድ ነበረብን ከዚያም አግድሞሽ በመሄድ ወደ ጠገዴ ተራሮች መውጫ ወደ ሆነው በአንድ ማሰፈያ መንገድ ወይም በር በኩል ማለፍ አሰብን:: መንገዱ ከፍታና ዝቅታ ያሰው ሲሆን ጥቅጥቅ ያሰ የቀርከሃ ጫካ ማቋረጥን ይጨምራል:: ሳሩም የአራት ሜትር ከፍታ ያለው የዝሆን ሳር ነው:: በመንገዳችን አንሰያ የተባሰውን ጥርት ያሰ ውሃ የሚፈስበትን ወንዝ ዘጠኝ ጊዜ አቋርጠናል:: መንገዱ እንደዚህ በየጊዜው የሚሰዋወጥበት ጉዞ ደስ የሚል ነበር፤ ሰውም ሆነ እንሰሳ የውሃ ጥሙን በፈለገ ጊዜ ማርካት ይችል ነበር::

ድንገት በደም የራሰ የልብስ ብጫቂ በመንገዳችን ላይ አየን:: ልብሱ የተገኘበት ቦታ ሳሩ ተደምድሞ የተረገጠ መሆኑ ያስታውቃል:: ግብ ግብ የተፈጠረበት ቦታ መሆኑ ምልክት ነው:: ብቻውን የአግር መንገዱን ተከትሎ ይሄድ የነበረ ወታደር ነው:: ምንም ሳይጠረጥር ጠመንጃውን ትከሻው ላይ አድርጎ ሲጓዝ አድፍጦ ይጠብቅ በነበረ ቀማኛ ጠመንጃውን ተነጥቆ ነው:: ከትንሽ ግብ ግብ በኋላ ወታደሩ ህይወቱን አሳልፎ ሠጥቷል:: አንግዲህ አስከሬኑ ወደ ጉድጓድ ተጥሏል ወይም አውሬ በልቶታል:: በአቢሲኒያ አንዲህ አይነቱ ነገር በየጊዜው ይፈፀማል:: አንደወጡ ቀሩ ለሚባሉ ሰዎች ምክንያት አንዱ ይህ ሳይሆን አይቀርም::

ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን ከሸሰቆው ዳርቻ ደረስን:: ከሚቀጥሰው ማረፊያ ካምፓችን ሰመድረሰ ወደ ላይ የአምስት መቶ ሜትር አቀበት መውጣት ነበረብን :: ከዚህ ካደርንበት ጋሞ ከሚባል ቦታ ላይ ሆኖ ዙሪያውን ለተመሰከተ ሰው ሸለቆውን በውስጡ ከሚጠማዘዘው ወንዝ ጋራ ከሸሰቆው ማዶ ደግሞ የአባት ተራሮችን ጨምሮ አሰገራሚ ትዕይንት ነው:: የተሰያዩ ቅርፅ ያላቸው አለቶችም ይታያሉ:: ለምሳሌ አንድ ከተራራዎች አናት ላይ ወጣ ብሎ አንድ ወጥ የሆነ የተሸሞለሞለ የድንጋይ ከፍታ ከተራራው አናት ይጀምርና ቁልቁል ወደ ሸለቆው ይወርዳል:: ሸለቆው ሲደርስ ይቋረጥና አንደገና በተቃራኒው በኩል ወደ ላይ ወደ ተራራው ተመልሶ ይወጣል:: ከፍታው ከአሰራአምስት አስከ ሀያ ሜትር ሲሆን የጎን ስፋቱ ግን ከሰስት ሜትር አይበልጥም:: "የንጉሡ አጥር" ተብሎ ይጠራል:: አፈ ታሪኩ እንደሚለው ከሆነ በንጉሡ ትእዛዝ ድንጋዩ አንደ አጥር በመነሳት ንጉሡንና ወታደሮቹን ከጠላቶቹ ከልሎ አስጥሏቸዋል ይባላል:: ይህን የድንጋይ ከፍታ በጠገዴ የተራራ ሰንሰለቶች በኩል ከታች ረባዳው ወልቃይት ገብቶ አስኪጠፋ



ድረስ ሲቀጥል አይቸዋለሁ:: በአይኔ ማየት የቻልኩትና የተከታተልኩት ይህ የአለት ከፍታ በግምት ወደ ሰባ ኪሎሜትር ይሆናል::

የሰስተኛው ቀን ጉዟችን ዳገት ብቻ ነው:: መንገዱ ወደ ላይ እያሻቀበ መሄድ ብቻ ነው:: አየሩም አየቀለሰ መሄድ ጀምሮአል:: አድካሚና አሰልቺ ነበር:: የተቀመጥኩበት በቅሎ መሸከም ሰላልቻለ በእግሬ መጓዝ ነበረብኝ:: ሁሰቱ የተጠበሱት ጋማ ከብቶች ደግሞ አስቸጋሪ ነበሩ:: ሙቀቱ፣ ላቡ፣ ወደኋላ የሚንሸራተተው የተሸከሙት ጓዝ ህመም አየፈጠረ ሰላስቸገራቸው አየደጋገሙ የተሸከሙትን ጓዝ በእርግጫ አየዘሰሉ ወይም መሬት ላይ አየተንከባለሉ አያወረዱ ይጥሉት ነበር::

ቀትር ላይ የሰስት ሺ ሜትር ከፍታ ላይ ያለ አምባ ላይ ወጣን:: ከአንድ ስአት ጉዞ በኋላም የደጃዝማች አያሌው ካምፕ ነው የተባለ ቦታ ደረስን:: ነገር ግን የፈለግሁትን ያህል ብሞክርም ካምፕ የሚባል ነገር ማየት አልቻልኩም:: ቦታው ትንሽ ዝቅ ብሎ ለአሩብ ኪሎሜትር የሚሆን ርቀት ተቀራርበው ባደጉ ትልልቅ ዛፎች የተሞላ ነው:: ይህ ካምፕ ከሆነ የሚንቀሳቀሱ ስዎች ማየት ነበረብን፤ በዚህ ቦታ ግን ዝር የሚል ነፍስ አይታይም::

ይህ ያልተሰመደ ነገር ነው ብዬ አሰብኩና ወደ አንደኛው ወታደር ዞር ብዬ ምን ማሰት ነው ብዬ ጠየቅሁት:: ወታደሩም ወደ አንድ ችፍግ ወዳለ ቁጥቋጦ አቅጣጫ አንድመለከት ጠቆመኝ:: በደንብ ሳስተውል የቁጥቋጦው ቅጠሎች አንደመድረቅ ያሉ ሰሰነበር ከሌሎቸ ሰየት ያለ ነው::

"ከቁጥቋጦው ብቅ የሚል ነገር አይታይህም ወይ" ብሎ ጠየቀኝ::

አ አሁን በግልፅ የጠመንጃ አፈሙዝ ታየኝ::

"ያ የአየር መቃወሚያ ነው:: ሰመሰወር ነው አንደዚያ የሆነው ዙሪያውን ካስተዋልክ አንደሱ የመስሉ ቁጥቋጦዋች በብዛት ታያሰህ" አለኝ:: ከዚያም ጨምሮ ሲያብራራልኝ በቀን ብርሃን ምንም አይነት አንቅስቃሴ ማድረግ ፈፅሞ የተከለከለ ነው:: "ሰውም ሆነ አንስሳ ጫካው ውስጥ መደበቅ አሰባቸው:: የጥልያን አውሮፕላኖች መምጣታቸው ስለማይቀር አስቀድመው እንዲያውቁብን ወይም አንዲያገኙን አንፈልግም::"

በአኔ መሪነት በሁሰት ረድፍ ተሰለፍን:: በዛፎች ስር ለስር ተራምደን ዋናው ካምፕ ደረስን:: ወታደሮች በሁሰት ረድፍ ተሰልፈው በተንጠቀቅ ቆመው አየጠበቁን ነበር:: ጥሩምባ ተነፋ፤ ስጦታም ከተሰጠን በኋላ ሰወር ብሎ ወደ ተወጠረ ደጃዝማች አያሌው ተጋድመው ወዳሉበት ድንኳን ውስጥ ገባን::

# ምዕራፍ አራት

## ሰላም በካምፕ ውስጥ

ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ በተሰያዩ አጋጣሚዎች ደጃዝማች አያሌውን ባያቸውም ትውውቅ አልነበረንም፡፡ ስለዚህ የዚህ የመጀመሪያ ግንኙነታችን ሥነስርአትና ትህትና በተሞላበት ሁኔታ አጭር ነበር፡፡

መቆያዬ ወደ ሆነው ድንኳን አሳዩኝ፡፡ ከላዩ በዛፎች ቅርንጫፎች ተከልሎ የተተከለ ትንሽና ደስ የሚል ድንኳን ነው፡፡ ሌላ ድንኳን ደግሞ ወደ ቁጥቋጦዎች ጠጋ ብሎ ስድሬሰሩና ስህክምና ቁሳቁሶች እንዲሆን ተብሎ ተተክሎአል፡፡

ፊሜን ከተላጨሁና ከታጠብኩ በኋላ  የካምፑን ዙሪያ ስማየት ወጣሁ፡፡ ድንኳን የተፈቀደው ለመኮንኖች ብቻ ስለሆነ የድንኳኖች ቁጥር መጠነኛ ነው፡፡ ጫካው ውስጥና በየዛፎች ስር ግን በቅጠል የተሰሩ ትንንሽ ጎጆዎች በሚያወሩና በሚስቁ ወታደሮች ተሞልተዋል፡፡ የሚያፀዱ ወይ ደግሞ በትንሽ የድንጋይ ወፍጮ ላይ የሚፈጩ ሴቶችም እሉበት፡፡ በቅሎ ፈረስና አህዮች ደግሞ የታጨደላቸውን አረንጓዴ ሳር እያኘኩ ባጭር ባጭሩ ታስረው ቆመው ይታያሉ፡፡ ለቋንጣ የሚሆን የሥጋ ዝልዝል ደግሞ በየቦታው ተንጠልጥሎ ይታያል፡፡ ሁሉም ነገር የሚመች ይመስላል፡፡ በጠቅላላው ካምፕ ውስጥ የተረጋጋ መልካም ምኞት ስሜት እንዳለ ይሰማኛል፡፡

በካምፑ ውስጥ እየተዘዋወርኩ እያለ የምልክት ጥሩምባ ተነፋ፡፡ ወዲያውኑ ካምፑ ውስጥ ህይወትና እንቅስቃሴ መታየት ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ፤ ሴቶች፤ አገልጋዮች ከተደበቁበት ቦታ ወጡ፡፡ የታሰሩት እንስሳትም ተሰቀቁ፡፡

ቀደም ሲል ያናገርኩት ወታደር ከቀኑ አሥራ አንድ ሰአት በኋላ የጣልያኖች አውሮፕላን በአየር ላይ ጥቃት ሥጋት የለም ብሎ ነገረኝ፡፡ ስለዚህ አሁን ወጥተው እንጨት መልቀም ውሃ መቅዳት ለከብቶቹም ሳር ማጨድ



ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ካምፑ ውስጥ እንደፈለጉት መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡ ለሚቀጥለው ቀን የሚሆነው ምግብ በሙሉ ዛሬ ማምሻውን መዘጋጀት አለበት፡፡ በጠዋት ቡና ብቻ ነው የሚፈላው፤ እሱም ቢሆን ፀሀይ ሳትወጣ ነው፡፡ በምንም አይነት በቀን እሳት አይነድም ምክንያቱም ጭሱ ከሩቅ በአየር መታየት ስለሚችል ነው፡፡ "እንደምታውቀው እሳት ባለበት ሁሉ ጭስ አለ" በማለት ወታደሩ ተናገረ፡፡

እንደዚህ ያለ የተጠናከረ ጥበቃ ሁኔታ በአቢሲኒያኖች መዘጋጀቱ አስገረመኝ፡፡ ከዚህ በፊት የአውሮፕላን ጥቃት ደርሶባቸው አያውቅም ለመሆኑ ማነው ይህን ያስተማራቸው ብዬ ጠየቅሁ፡፡

"ጀግናው ጌታችን ደጃዝማች አያሌው" የሚል መልስ ተሠጠኝ፡፡ "እኛ የምናውቀው ነገር የለም፤ አውሮፕላን የሚባል ነገር እንኳን ገና አላየንም ነገር ግን አለቃችን እንደሚያውቁ ስለምናውቅ የታዘዝነውን መፈፀም ነው፡፡ ዋ! ትዕዛዙን ስማያከብር ሰው ከሙሉ ጦር ፊት አርባ ጅራፍ ነው የሚወርድበት"

ደጃዝማቹን እየወደድኳቸው መጣሁ፡፡ ጉልበትና ጥንካሬ ያለው አንድ ሀበሻም አለ አልኩ፡፡ እንግዲህ የቁርጥ ቀን ሲመጣ ወደኋላ ሳይሉ ገትረው የሚይዙ ሰው መሆናቸውን ደግሞ አናያለን አልኩ፡፡ የቁርጥ ቀን ሲመጣ መሸሽ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡

አገልጋይ ልጅ መጥቶ ወደ ደጃዝማች ድንኳን እንደተጠራሁ ነገረኝ፡፡

ደጃዝማች አልጋቸው ላይ ግማሽ እንደመቀመጥ ብለው ከፊት ለፊታቸው ጠረጴዛ ተቀምጦ አየሁዋቸው፡፡ ወድያውኑ ምርመራ እንዳደርግላቸው ጠይቄ ተፈቀደልኝ፡፡ ምርመራው እንዳለቀና መድሃኒቱም ተሠጥቶ እንደጨረስን እጃችን ታጠብንና ወደ ምግብ ገበታ አመራን፡፡

የሚገርም የምግብ አይነት ነው የቀረበው፡፡ አውሮፓዊ እንደመሆኔ ምንም አውሮፓን ባያዩና ለሥልጣኔ የራቁ ቢሆንም ለኔ የሚሆን የፈረንጅ ምግብ ማዘጋጀት እንደሚቻል ስማሳየትም ነው፡፡ ለካስ ከጣልያኖች ቤት ይሠራ የነበረ አገልጋይ ያየውንና የተማረውን የአውሮፓ ምግብ እንዲሰራ ሙሉ ፈቃድ ተሠጥቶት የሚያውቀውን የምግብ አይነት በሙሉ አዘጋጅቶአል፡፡

የምግቡ አይነት ደግሞ በሚቀጥለው ተራ ቀረበ፡፡ የዶሮ ስጋ፤ ሳርዲን በዘይት የተጠበሰና ከነመን ጋራ የተዘጋጀ፤ የሩዝ ቅቅል ከተምር ጋራ፤ የተቀቀለ የበሬ ስጋ ከሩዝና ከድንች ጋራ፤ የታሸገ ሳልመን (የአሳ ዝርያ) ከተቀቀለ ካሮት ጋራ ሌሎችንም ጨምሮ፤ በመጨረሻም የታሸጉ የተቀላቀሉ ፍራፈሬዎች ነበሩ፡፡

የምግብ አምሮትም ስለነበረኝ ከቀረበው ሁሉ እየቀማመስኩ ምግቡን ያዘጋጀውን ሰው እያመሰገንኩ የበላሁትን በጥሩ የኢጣልያ ወይን አወራረድኩት:: ከዚያም ቀስ ብዬ ጋባዤን የአቢሲንያ ምግብ እንድቀምስ እንዲፈቀድልኝ ጠየኩኝ::

"እንዴታ:: ምን አለበት፤ ነገር ግን ከወደድከውና ከቻልከው ነው ተባልኩ::"

"በሚገባ" አልኩ ቀጠል አድርጌም "ሌላ ነገር ሳይሆን እንጀራና ወጥ ነው የምበላው::" ብዙ ጊዜም ደጋግሜ ስለበላሁት እንደምወደው የውነቱን ተናገርኩ:: ከዚያ በኋላ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር የፈረንጅ ምግብ እንዳይሰራ እኔም የሐበሻ ምግብ እንድበላ ተስማማን::

ተመግበን እንደጨረሰን ደጃዝማች ሻምፓኝ ከፈቱልኝ:: እንኳን ደህና መጣህ አቀባበል ነው:: ቀጥሎም የአገሩን ቋንቋ መቻሌ የአገሩን ባህል በማክበሬ በጣም የረኩ በመሆኑ "ደስ ያሰኘኛል" አሉ "ምክንያቱም አሥራ አምስት ሺ ከሆኑት በኔ ሰዎች መሀል አንግድነት አይሰማህም" በማለት ገለፁ::

እኔም ከልባቸው እንደተናገሩ ነው የተሰማኝ ወደፊት በስንት መከራ የሚፈተሸው ወዳጅነታችን በዚህ ምሽት ተጠናክሮ ነው የተጀመረው::

እኩለ ሌሊት እስከሚሆን ቁጭ ብለን በጋራ ስለምናውቃቸው ሰዎች ማውራት ቀጠልን:: ደጃዝማች በአዲስ አበባና በውጭ አለም የሚሆነውን ማወቅ እንደሚፈልጉ ግልፅ ነው:: ስለሁኔታዎች ያላቸው አውቀትና ግንዛቤ የሚገርምና ከአንድ ኢትዮጵያዊ ከሚጠበቀው በላይ ነበር:: የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሳን ስንወያይ ደስተኛ ነበርኩ::

ለመሄድ ስነሳም ስለካምፑ ምን አስተያዬት እንዳለኝ ጠየቁኝ::

"አስገራሚ ነው እነደእውነቱ ከሆን እንደዚህ አይነት ዝግጅት አልጠበቅሁም" አልኩኝ

"መልካም! እየህ" አሉ "እነዚህ አውቀት የሌላቸው ወታደሮች ስለዘመናዊ ጦርነት የሚያውቁት ነገር የለም:: ቦምብ ከሰማይ ሲጣል አይተው አያውቁም:: ቦምብ የሚያደርሰው የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሚሆን ግምቱም የላቸውም:: ሀሳብ የላቸው ግደ የለሽም ስለሆኑ አንግዲህ በኔ ነው የሚተማመኑት:: ሃላፊነቱ የኔ እንደመሆኑ መጠን የግድ ሀይለኛ መሆን አለብኝ:: በጠላት አስቀድሜ ሳልታይ የጦር ግንባር መድረስ እንዳለብኝ ትረዳለህ::"



እዎ ግን ይህን ያህል ቁጥር ያለው ሠራዊት ከሴቶች ከልጆች እና እንስሳቱን ጨምሮ ሳይታይ እንዴት ነው 250 ኪሎሜትር ርቀት የሚጓዘው አልኩኝ::

"መሄድ አለበት እናም ይሄዳል" አጭር መልስ ነበር::

ተሰናብቼ ወደ ድንኳኔ አመራሁ:: ይህ ብልህና ጠንካራ ሐበሻ ሰው አስደንቆኛል:: አመለካከታቸውና አቀራረባቸው አውሮፓዊ ሰው ነው የሚያስታውሱኝ:: ቁመናቸው ከመካከለኛ ቁመት በላይ የተሟላ የተደላደለ ሰውነት ሲኖራቸው ወፍራምም አልነበሩም:: ፀጉራቸው ጨብረር ያለ ሲሆን ፊታቸው እንደከብነት የቃጣውና አጠር ያለ በሥነ ሥርአት የተቆረጠ ፂም አለበት:: ግንባራቸው ሰፋ ያለ ሲሆን አይናቸው ገለጥ ያለ አመለካከት ከፈገግታ ጋር ያሳያል:: ሃምሳ አመት ዕድሜ ያለፋቸው በቅርቡ ነው::

ለሀያ አምስት ቀናት ቆይታ ባደረግንበት በዚህ ቦታ የደጃዝማች ጤንነት በየቀኑ እየተሻሻለ ሲሄድ ማየት አርከቶኛል:: ሐበሻ ሲታመም የፀሐይ ብርሃን ሆነ ሌላ ብርሃን እንዳይጥልበት ራሱን ዘግቶ ነው የሚቀመጠው:: ብርሀን ሲጥል አደገኛ ነው ተብሎ ነው የሚታመነው:: በጨለማው ምክንያትና በታሸገው አየር ምክንያት በሽታው እየከፋ በመሄድ የማገገሚያ ጊዜው ይራዘማል:: ከመጣሁ በሶስተኛው ቀን ግን ለአንድ ሰአት የሚሆን ውጭ ወጥተው በመቀመጥ ንፁህ አየር እንዲያገኙ አሳመንኳቸው:: ከዚያ በፊት ደግሞ የድንኳኑ በር እንዲከፈትም መከሬ ይከፈት ጀመር:: ውጭ ወጥተው በብርድ ልብስ ተሸፍነው የሚመች ወንበር ላይ መቀመጡን እየወደዱት ስለመጡም ቀኑን በብዛት በዚህ መልክ እንደተቀመጡ አሳለፉት:: ብዙ ጊዜ እንቅልፍ ያስቸግራቸዋል፤ ያን ቀን ማታ ግን እንደወደቀ ግንድ ጥሩ እንቅልፍ ተኝተው እንዳደሩ በነጋታው ነገሩኝ::

በነዚህ ቀናትም እኔም የካምፑን አኗኗር ለማጥናት አጋጣሚ አገኘሁ:: ከብዙዎች የደጃዝማች መኮንኖችና አዛዦችም ጋራ ተዋወቅሁ:: የመኮንኖችን የጀግንነት ታሪኮችና ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት እሰማ ነበር:: ሁሉም በደጃዝማች ዕድሜ ክልል ያሉ ሲሆን በአሥራ ስድስት አመታቸው አፄ ሚኒሊክ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው የከፋ ገዥ ካደረጓቸው ጊዜ ጀምሮ አብረው ያገለገሉ ናቸው:: በብዙ ጦርነቶች ጎን ለጎን አብረው የተዋጉ ሲሆን ለነዚህ ሁሉ አመታት በድል ሆነ በውድቀት ሳይለያዩ አብረው የቆዩ ናቸው:: ቆራጥና የማያወላውሉ ወንዶች ናቸው እኔም በቀላሉ ወደድኳቸው::

በተጨማሪ ከደጃዝማች የንስሐ አባት አባ ጌታሁን ጋራ ተዋወቅን፡፡ አባ ጌታሁን የዳባት ቤተክርስቲያን አለቃ ሲሆኑ ሀብታምና ተሰሚነት የነበራቸው ናቸው፡፡ መልካቸው እንደ ሥዕል የጠራ የሚያምር ነው፡፡ የሚያሳዩት እንገት የደፋ አመለካከት ቢሆንም በውስጣቸው ኩራት እንዳለባቸው ያስታውቃል፡፡ ሁለታችን ግን ልብ ለልብ አልተገናኘንም፡፡ እኔ ያሰብኩዋቸው እንደ አስመሳይ አድርጌ ሲሆን እሳቸው ደግሞ እምነት የለሽ ወይም ፀረ ሀይማኖት አድርገው ነው የሚያስቡኝ፡፡ ሁለት የማይገናኙና የማይተማመኑ አመለካከቶች ናቸው፡፡

ጥቅምት ሀያ ሶስት ንጉሡ የነገሱበት ቀን ነበር፡፡ ቀኑን በማክበር ለአምስት ሺ መኮንኖችና ወታደሮች ግብር ሊደረግ ነው፡፡ ሁለት ትልልቅ የሾላ ዛፎችን እንደጣራ በማድረግ በእንጨትና በቅጠል የታጠረ በአንድ ጊዜ አንድ ሺ ሰዎች ማስተናገድ የሚችል ዳስ ተሠራ፡፡ የአካባቢው ገበሬዎች ከበአሉ በፊት አምስት ሺ እንጀራና ሃምሳ ጋን ጠላ እንዲያቀርቡ ግብር ተጥሎባቸው ነበር፡፡ የደጃዝማች እያሌው ወጥ ቤቶች በየጦር ግንባሩ አብረው የሚጓዙ ስላሳ የሚሆኑ አገልጋይ ሴቶች ያሉበት ሲሆን ለድግሱ የሚያስፈልገውን ጠጅና ወጥ እንዲያዘጋጁ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

አዳራሹ ውስጥ ለዝቅተኛ መኮንኖችና ለባለትዳር ወንዶች የተለየ ማዕድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንደጠረጴዛ ሆኖ የተሠራው ከሥር በተተከሉ ጉራጅ ግንዶች ላይ የተዘረጋ የቀርከሃ ሳጠራ ነው፡፡ ርዝመት ያለው ሲሆን ስፋቱ ከግማሽ ሜትር አይበልጥም፡፡ ላዩ ላይ እንደጠረጴዛ ልብስ ሸማ ተዘርግቶበታል፡፡

በአዳራሹ በአንድ በኩል ደግሞ ከፍ ያለ መድረክ ተዘጋጅቷል፡፡ ላዩ ምንጣፎች ተዘርግተውበታል፡፡ የአለቃው የደጃዝማች መቀመጫ ተለይቶ ይታወቃል ምክንያቱም ምርጥ ምንጣፍ የተዘረጋበትና ሁልጊዜ የሚቀመጡ ሁለት ትራሶች ስላሉበት ነው፡፡

ሞሰቦች ደግሞ በሚገባ ርቀት ተሰልፈው ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ደግሞ ለተከበሩ እንግዶቸ ማዕድ መሆናቸው ነው፡፡ የደጃዝማች ቦታ ላይ ሞሰብ አልተቀመጠም፡፡ ደንቡ ሞሰቡ የሚመጣው ደጃዝማች ከተቀመጡ በኋላና ሞሰቡ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሚደረገው በምግቡ ላይ መርዝ እንዳይደረግ ለመጠበቅ ነው፡፡ በአቢሲኒያ በዚያን ጊዜ ሰዎችን መመረዝ ደጋግሞ የሚታይ ነገር ነው፡፡ እንደሳቸው ከፍ ያለ ሥልጣን ወይም ማዕረግ ያለው ሰው ከምቀኛና ከጠላቶች ሁል ጊዜ መጠንቀቅ አለበት፡፡



ሁሉም ከተዘጋጀ በኋላ ደጃዝማች በጥቂት አገልጋዮች ታጅበው ወደ አዳራሹ ገቡ፡፡ ከሳቸው ቀጥሎ ደግሞ የክብር እንግዶች ወደ ውስጥ እንዲገቡ ተጠሩ፡፡ የክብር እንግዶችን ተከትለው የንስሐ አባትየው ገቡ፡፡ ሁሉም በደጃዝማች ግራና ቀኝ በኩል ተቀመጡ፡፡ ለእያንዳንዳቸው ከፊት ለፊታቸው የተከደኑና የተሸፈኑ ሞሰቦች ተቀምጠዋል፡፡ ሁሉም ተጋባዦች እንደማዕረጋቸው እየገቡ ተቀመጡ፡፡ ከደጅ በኩል ውሀ በማስታጠቢያ ይዞ የቆመ አገልጋይ ስለነበር ሁሉም ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን ታጥበዋል፡፡

ደጃዝማች ምልክት እንደሰጡ ዋናው አሳላፊ በንፁህ ጨርቅ ላይ የተቀመጠ እንጀራ ይዞ ገባ እሱን ተከትለው ሌሎች አሳላፊዎች የቀረውን ምግብና መጠጥ ይዘው ገቡ፡፡ ሁሉም እንግዶቸ ከተቀመጡበት ተነስተው ቆሙ የደጃዝማች ሞሰብ ከቀረበና ከተከፈተ በኋላ የንስሐ አባትዬው የቡራኬ ፀሎት አደረጉ፡፡

አሳላፊውም እንጀራውን ቆርሶ ከየወጡ አይነት ካራሰ በኋላ ሞሰብ ላይ አስቀመጠ፡፡ ደጃዝማችም ከእያንዳንዱ ቁራሽ ትንሽ ጉርሻ እያነሱ አሳላፊውን አጎረሱት፡፡ ለሳቸው የሚቀርበው ምግብ አይነት መርዝ እንዳይደረግበት ሐላፊነቱ የራሱ የዋናው አሳለፊ ነው፡፡

ደጃዝማች መብላት ጀመሩና ለሌሎችም ምግብ እንዲጀምሩ ምልክት ሠጡ፡፡ ሌሎች ተጋባዦች የቀረበላቸውን ሞሰብ እየከፈቱ መብላት ጀመሩ፡፡ የነሱ ሞሰብ እንጀራና ወጡ አንድ ላይ ስለቀረበ ሳይቆዩ ወዲያውኑ መመገብ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የጠጅ አሳለፊው ጠጅ በማንቆርቆርያ ይዞ ቀረበና ለደጃዝማች ከመቅዳቱ በፊት ራሱ መጀመሪያ መቅመስ ነበረበት፡፡ ስለዚህ በእፍኙ ላይ ትንሽ ከቀዳ በኋላ ፉት አድርጎ ጠጣ፡፡ ጠላውም እንደዚሁ ለእንግዶቹ ይቀርብ ጀመር፡፡

ደጃዝማች ትንሽ ከበሉ በኋላ በር ላይ የቆመውን ሌላ ዋና አሳለፊ የትኞች እንግዶች ናቸው ወደ ውስጥ ያልገቡ ብለው ጠየቁ፡፡ ዋናው አሳለፊ የእንግዶችን ስምና ማዕረግ በደንብ ማወቅ አለበት አዲስ የመጡ ቢሆንም፡፡ ተከትሎም ደጃዝማች ውጭ የቀሩትን እንግዶቸ ማን ማንን ተከትሎ እንደሚገባና እንዴት እንደሚቀመጥ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ አቀማመጥ ትልቅ ነገር ነው፡፡ አንድ እንግዳ በስህተት ያልሆነ ቦታ ወይም እንደማዕረጉ ካልተቀመጠ እንደስድብ ነው የሚቆጠረው፡፡

ሰዎቹ በቦታቸው እንዲቀመጡ በሚደረግበት ጊዜ ሌሎቹ ተራ አሳለፊዎች እንጀራና ወጥ በጠረጴዛው ላይ ማስቀመጥ ቀጠሉ፡፡



ደጃዝማች አያሌው ብሩ (ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ)





ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከጦር አለቆቻቸው ጋር(ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ)

ከውጭ በኩል ደግሞ ከፍ ያለ ግርግርና የጩኸት ድምፅ ይሰማ ጀመር:: ወደ ውስጥ ለመግባት ከሚጋፉት ወታደሮች ነበር የመጣው:: እርቧቸዋል እንደገና ደግሞ ምግቡ እነሱ ሳይደርሳቸው ያልቃል የሚል ፍራቻም አለባቸው:: ሁለት በትር የያዙ ጠንካራ በር ጠባቂዎች በመግቢያው ግራና ቀኝ በኩል ቆመው የሚገባውን ሰው ይቆጣጠራሉ::

ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ግብር ሲጣል ያላየ ሰው ቀጥሎ የሆነውን ነገር መረዳት ይቸግረዋል::

ግርግርና ጫጫታው ተቀይሮ ወታደሮቹ እየተጋፉ ወደ እዳራሹ ዘለቁ:: እርስ በራሳቸው እየጮሁና እየዘለሉ አንዱ በአንዱ ላይ መጋፋት ቀጠሉ:: በትር የያዙት ጠባቂዎች በዱላቸውና በእጃቸው ዳሱን ጥሶ የሚገባውን ሰው በተቻለ አቅም ገፍተው ለመያዝ ይታገላሉ:: በእንደዚህ እይነት ግርግር ዱላው የት እንደሚያርፍም አይታወቅም:: ጭንቅላት ይፈረከሳል፡ አይን ይፈሳል፡ መሬት ላይ የወደቁ ሰዎች ደግሞ ተረግጠው ህይወት ማለፍም ይደርሳል::

ያለው ቦታ በሙሉ በእንግዶች ተይዞ ሲያልቅ ውጭ የቀሩት ውሰጥ የገባው በልቶ እስኪወጣ ድረስ ተራቸውን የግድ መጠበቅ አለባቸው ::

በአጭር ጊዜ ውስጥ አንጀራና ወጡ ድራሹ ይጠፋል:: ቀጥሎ የሚቀርበው ወይም ሁሉም የሚጠብቀው ዋናው ምርጥ ምግብ ጥሬ ሥጋ ነው::

ጥሬ ሥጋው እስከሚቀርብ ጠላ በማንቆርቆርያና በብርሌ ይሠጣል:: ጥሬ ሥጋውን ደጃዝማችና ታላላቅ እንግዶች ይጀምራሉ:: ምርጥ ብልት እየተቆረጠ ይቀርብላቸዋል:: ሥጋውም በደንብ ከደለበ ከብት ነው የሚሆነው:: ሌሎች ወታደሮች ሥጋው ከማንኛውም ከብት ይምጣ ብቻ የተሠጣቸውን ብቻ መብላት ነው::

ሥጋውን ተሸክመው የሚዞሩ አገልጋዮች ናቸው:: ሥጋው በብልት በብልት ነው የሚቆረጠው:: እኩል እኩል ድርሻ እንዲደርሳቸው ይደረጋል:: አንዱ ድርሻ ለአምስት ሰው እንደሚሆን እየሆነ ነው የሚሠጠው:: ስለዚህ አንድ ሰው በግምት አምስት ኪሎ የሚሆን ሥጋ ይደርሰዋል ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ እንድ በሬ ከሃምሳ እስከ ሰልሳ ወታደሮች ይመግባል ማለት ነው:: እያንዳንዱ ሰው አገልጋዮች አንጠልጥለው ከያዙት ሥጋ በቢላዋ የእጅ ጭብጥ የሚያህል ከቆረጠ በኋላ ለጉርሻ የሚበቃውን ያህል በጥርሱ ነክሶ ይዞ በያዘው ቢላዋ ከስር ወደ ላይ ከጥርሱ እስጠግቶ ይቆርጣል:: ይህ አይነቱ አበላል ልምድ ይጠይቃል እለዚያ ከንፈርን ጨምሮ የአፍንጫን ጫፍ መቁረጥም ሲያስከትል ይችላል::



መጀመሪያ ላየው ሰው የጥሬ ሥጋው ሽታ በተጨማሪ የአውሬ ያህል አፍጥጠው ጥሬ ሥጋውን የሚበሉትን የአቢሲኒያ ሰዎች ማየት በጣም የሚያስፈራ ነበር:: የኋላ የኋላ ግን እኔም ራሴ መብላት ለመድኩና ጭራሹን እየወደድኩት መጣሁ:: ለጦርነት ከወጣን ወዲህ ቫይታሚን በሚጎላቸው የምግብ እይነቶች ተወስነን መከረም የግድ ነው:: ሰለዚህ እንደዚህ አይነት የሥጋ ምግብ በማግኘት ጤንነታችን ተጠብቆ መቆየት ይቻላል::

በአቢሲኒያ ታሪክ ጥሬ ሥጋ መብላት የቆየ ጥንታዊ ባህል እይደለም:: የተጀመረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ[1] ወረራ ጊዜ ነው:: በጣም አክራሪና ጨካኝ ስለነበር ክርስቲያኖችን እያሳደደ ሀይማኖታቸውን ከደው የሱን እምነት ካልተቀበሉ ያሰቃይና ይገላቸው ነበር:: ሰለዚህ የአቢሲኒያ ሰዎች የግድ መሸሽና በየተራሮችና በየጫካዎች መደበቅ ነበረባቸው:: ለመኖር ደግሞ ይዘዋቸው የሄዱትን የቤት እንስሳት መመገብ ነበረባቸው:: ተደብቀው ሰለሚኖሩ ግን እሳት ማንደድ አይችሉም:: ሰለዚህ የግድ ጥሬ ሥጋ መመገብ መጀመራቸውና መልመዳቸው የሚያስገርም አይሆንም:: ቀላልም አማራጭ ነበር፤ እሳት እያሰፈልግ ማብሰያ ቁሳቁስ እያስፈልግ:: እንሰሳው ወዲያው እንደታረደ ጠጋ ብሎ ምግብ መጀመር ይቻላል:: በስንፍና አመለካከት ቢሆን ያለድካም በቀላሉ የሚገኝ ነገር ሁልጊዜ ጥሩ ነው:: ጣዕሙም ቢሆን ጥሩ ነው:: እንግዲህ በአቢሲኒያ ከዚህ በመነሳት ነው ጥሬ ሥጋ ተፈላጊ የምግብ እይነት የሆነው::

የሆኖ ሆኖ ይህ ምግብ ደግሞ የራሱ ጉዳትም አለው:: ያም በኮሶ በሽታ መያዝ ነው:: ሁሉም ዕድሜያቸው ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው እቢሲኒያውያን ቅድመ አያቶቻቸውን ጨምሮ ኮሶ እለባቸው:: በኮሶ ያልተያዘ ሰው ይኖራል ብለው አያስቡም:: እንግዲህ በኮሶ ያልተያዘ ሰው ቢኖር ከጤነኛ ሰውም አይቆጠርም:: ውቃቢው ጥሎት ሄዷል ነው የሚሉት:: በነሱ እስተሳሰብ የኮሶው ትል እንኳን ሰውየውን ማወቅ ወይም መቀበል አልፈቀደም::

---

*1. ግራ እጅ ስለሚጠቀም "ግራኝ አህመድ" ኢትዮጵያኖች የሠጡት ስም ነው:: ሙሉ ስሙ አህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ ነው:: በ1506 -በ1543 እኤአ፤ በልጅነቱ የወታደራዊ ሥልጣናም ኢዮርን ነበር:: የእስልምናን ሀይማኖት በሠይፍ በኢትዮጵያ እንዳስፋፋ ይነገርለታል:: በጎንደር ደምቢያ የሚባል ቦታ የግራኝ አህመድ ዋና ካምፕ ነበር:: (ከተለያዩ መረጃዎች የተዘገበ)*

የኮሶው ትል ከመጠን በላይ እንዳያድግ ለማድረግ በየሁለት ወሩ መድሃኒት ይወሰዳል:: ተወላጆቹ ብዙ ከአፅዋት አይነቶች መድሃኒቶች የሚጠቀሙ ቢሆንም እንደኮሶ ዛፍ በብዛት የሚጠቀሙት የለም:: የዚህ ዛፍ (ሃገኒያ አቢሲኒካ Hagenia Abyssinica) ፍሬውም ሆነ አበባው ለጥቅም ይውላል:: ይህ ተክል ከባህር ወለል ከ2500 ሜትር ከፍታ በታች ጭራሽ አይበቅልም:: ስለዚህ መድሃኒቱ ከገበያም ይገዛል ወይም ተክሉ ከሚያድግበት አካባቢ ቀጥታ ይለቀማል:: ለአንድ ሰው ለመድሃኒት የሚሠጠው የእጅ ጭብጥ የሚያህል ሲሆን መድሃኒቱ ከውሃ ወይም ከማር ጋራ ተለውሶ ይደቆስና በጠዋት በባዶ ሆድ ይወሰዳል::

የኮሶ መድሃኒት ሀይለኛም ነው ሆድ ቁርጠትና ሠገራ የግድ ነው የሚመጣው ብዙ ጊዜም ማጥወልወል ያስከትላል:: ሐይለኛ የሠገራ መመላለስ ቢያመጣም ጠቅላላው ትል እንዳለ ከነጭንቅላቱ እልፎ እልፎ ነው የሚወጣው::

የኮሶ መድሃኒት መውሰድ እንደተቀደሰ ስርአት ስለሚቆጠር ሥርአቱን ማደናቀፍ ወይም መረበሽ አይቻልም:: መድሃኒት ከመወሰዱ ከአንድ ቀን በፊት ሰውየው ጓደኞቹን ይሰናበታል:: በሚቀጥለው ቀን በጥዋት መድሃኒቱን ሲወስድ መድሃኒቱን ያዘጋጀው አንድ ሰው ብቻ ነው አብሮት የሚሆነው:: ከዚያ በኋላ ብቻውን በር ዘግቶ ይቀመጣል:: ሙሉ ቀን ከቤተሰብ በስተቀር ሌላ ሰው ዝር አይልም አለበለዚያ ጥላ ይጥልበትና መድሃኒቱ ይረከሳል ወይም አይሰራም ይባላል:: ይህ የጥላ ነገር የመጣው ቤቱ አንድ መግቢያ ብቻ ስላለው ብርሃን የሚገባው በዚያ በኩል ስለሆነ ሰው ከጋረደው ብርሃኑ ስለሚሸፈንም ነው:: ጥላ አደገኛ ነው ተብሎ የሚታመነው:: ስለዚህ ነው ጠያቂ ሳይመጣ ብቻ መሆን የሚፈለገው::

በሌላ በኩልም ቢሆን የኮሶ መድሃኒት ሲወሰድ የሚደረገው ሥርአት ሌላ ጠቀሜታ አለው:: *(ዶክተር ሀነር ለህክምና ባለሙያዎች ማህበር በዚህ ጉዳይ ላይ ባደረገው ንግግር ትክክለኛ ነበር)*:: ጉዳዩ እንግዲህ የኮሶ መድሃኒት የወሰደን ሰው ምንም አይነት ትዕዛዝ ወይም ሥራ መስጠት አይቻልም:: በማንኛውም የሥልጣን ሀላፊነት ወይም ደረጃ ላይ ቢሆን የኮሶ መድሃኒት ከወሰደ ፈቃድ ይሠጠዋል:: የአቢሲኒያ መንግስታዊ ሥራ በዚህ በኮሶ መድሃኒት ምክንያት ምን ያህል እንደሚስተጓጎል ለማንም ግልፅ ነው:: አገረ ገዥ፤ ሚኒስትር፤ አሽከርና አገልጋዮችን ጨምሮ የኮሶ መድሃኒት በየጊዜው በመውሰድ ሰብቻቸው ተከልለው ማንም ሳይረብሻቸው በሰላም ሲያጥወለውላቸው ይውላሉ::



# ምዕራፍ አምስት

## አያሌውን ተከተልኩ

ጥቅምት ሀያ ስድስት ከጋሞ ካምፕ ተነሳን:: በሰሜን በኩል አስር ኪሎ ሜትር ርቀት ወደሚገኝ አዲ እትየ የሚባል ቦታ ለመጠጋት ነው:: በብዙ በተለያዩ ምክንያቶች በዚህ ቦታ ላይ ለብዙ ሳምንታት እንድንቆይ ሆነ:: የመጀመሪያው ምክንያት ሁሉም ሠራዊት ተጠቃሎ አንድ ላይ አልገባም:: እንቅስቃሴው ገና እየተጀመረ ነበር እና ግማሹ ዘማች ከቤቱም አልወጣም::

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከታች በቆላው የወባ በሽታ እየገነነ ነበር የዝናቡ ወራት እያለቀ ስለነበር ትግራይና የተከዜ ወንዝ ደግሞ የሚያቋርጡት ሆኖ አልተገኘም:: የሞላው ወንዝ መጠን እየወረደ እንደሆነም ወሬ ተነገረን::

ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ ከአዲስ አበባ በመጣ ቴሌግራም ደጃዝማች አያሌው በየትኛው አቅጣጫ ወደ ግንባር እንደሚሄዱ አዲስ ትዕዛዝ እስከሚመጣ ድረስ እንዳይንቀሳቀሱ የሚል ነው:: የመጀመሪያው ትዕዛዝ በኤርትራ ምዕራባዊ ድንበር በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ ሱዳንን ወደ የሚያዋስነው ሰቲት ወደ ተባለ ቦታ እንድንሄድ ነበር:: እንግዲህ ያ የዘመቻ እቅድ በአዲስ አበባ ታጥፏል ማለት ነው ምክንያቱ ለኛ አልተነገረንም:: ቆይተን ነው ያወቅነው::

አዲ አትየ ደስ የሚል ቦታ ነው ተራሮችና ጫካ አረንጓዴ ሜዳዎች ሞልተዉታል:: የድሮ ገዳም ፍርሥራሽ ያለበት ከፍታ ቦታ ለዋናው ካምፕ እንዲሆን ተመረጠ:: ያረጁ ትልልቅ ዛፎች ቅርንጫፎች ሽፋን ስለሚሰጡ ድንኳኖችን ከስር ተክለን እንደሚመቹን ለማድረግ ቻልን::

የደጃዝማች መኖርያዎች ሶስት ውድ የሆኑ በተርታ የተተከሉ ድንኳኖች ሲሆኑ አንደኛው ለአንግዳ መቀበያ አንደኛው ለምግብ ሶስተኛው ደግሞ ለመኝታ ነበር::

መኮንኖችና ወታደሮችም ድንኳናቸውን በቡድን በቡድን ዙርያውን ይተከሉ ጀመር አዲስ የሚቀላቀለው ጦርም እንደዚያው እየተከለ ካምፑ ዙርያውን በብዙ ማይል የሚቆጠር ርቀት ድረስ ሆነ::

የጦሩን ቁጥር መገመት አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም አጠገብ ከሰፈረው በስተቀር ሌሎች ተደብቀው ነው የሰፈሩት እኔም ማየት አልቻልኩም::

የአቢሲኒያ የጦር መሪ ሌላ ጊዜ ካምፑን ከፍት መሀል ሜዳ ላይ ያደርግና ወታደሮቹን በዙሪያው እንዲሰፍሩ በማድረግ ቁጥሩን በማወቅ ከጠላቱ ጦር ቁጥር ጋር ያወዳድራል:: በዚህ ቦታ ግን የጦር መሪው የጦሩን ቁጥር ማወቅ ሆነ ማሳየት አይችልም::

በአዲ አትየ ቆይታችን በመጀመሪያዎቹ ቀናት ስአዲስ አበባ መንግስት ቴሌ ግራም ልኬ ነበር፤ እሱም በውላችን መሠረት ደጃች አያሌው ሙሉ በሙሉ ተሽሏቸው ስለሚገኙ አውሮፕላን ተልኮልኝ እንድመለስ ነበር:: ደጃዝማች አብሬ እንድቆይ ይፈልጉ ስለነበረ ቴሌ ግራሙን እንድልከና እንድጠይቅ እያመናቱ ነበር የፈቀዱልኝ::

አውሮፕላን እስኪላከልኝ በምቆይበት ጊዜም ጊዜዬን የማሳልፈው ጥዋት ጥዋት ሕሙማንን በማየት ነበር:: ሰዎች መሄዴን ሲሰሙ ያለ የሌለ ህመም ይዘው መቅረብ ጀመሩ:: ከሁሉም በላይ ብዙ ጥርስ ነቀልኩ፤ ይህም ተደምሮ ስሰባት አመታት ስሰራ ካወለቁት በላይ ነበር:: ወታደሮች ሌላው ቀርቶ የታመሙ ከብቶቻቸውን ይዘው መምጣት ጀመሩ:: የከብት ህክምና ትምህርት ስላልነበረኝ ይህንን መከራከሪያ ምክንያት አቀረብኩኝ:: "እኔ የሰው ዶክተር ነኝ:: እህያህን ዛሬ ባከምልህ የአህያ ዶክተር እሆናለሁ እና ወደፊት ደግሞ አንተን አሞህ ባከምህ የአህያ ዶክተር ስለሆንኩ አንተም እንደአህያ ነው የምትቆጠረው::"

ይህ ብልሃት ሠራ ምክንያቱም ስህገሬው ሰዎች ከትልቁ ሰድብ አንዱ አህያ መባል ነው::

ምሳ ከደጃች አያሌውና ከሌሎችም ጋራ ከበላሁ በኋላ የማውቃቸውን ሰዎች ለመጠየቅ ወይም ህሙማኑን ለመጠየቅ ወጣ ብዬ እዘዋወራለሁ:: እንደዚህ በእግሬ በምዘዋወርባቸው በአንዱ ቀን ለሕይወቴ የሚያሰጋ ነገር መኖሩን ተረዳሁኝ:: ወደ ጦር ግንባሩም እየተጠጋን በሄድን ቁጥር ይህ ለኔ የሚያሰጋኝ ነገር እየጨመረ እንደሚሄድ እርግጠኛም ሆንኩ::

ወታደሮች አካባቢ እሰፍ ብዬ ስሄድ የምሰማው ንግግር "ይሄ ነጭ ሰው እዚህ ምን ያረጋል? ነጭ ሰው እዚህ ምን ሲረባ ነው? ነጮች እርስ በእርስ



ይተጋገዙ የለ እሁን ደግሞ ጦርነት ላይ ስለሆን እየሰለለም ይሆናል:: በጊዜ ማሰውገድ ነው የሚበጀው:: ብቻ ጦር ሜዳ እንድረስ እንጂ ጥይት ከየት አቅጣጫ እንደተተኮሰ ማን ያውቃል::"

አልፎ አልፎ ደግሞ "ዝም በሉ! ጮሃችሁ አትናገሩ፤ እኛ አገር ስለተወሰደ ቋንቋችንም ይናገራል" የሚል ንግግር እሰማለሁ::

ብዙ ጊዜ ደግሞ ሰዎች በፊት ለፊት ይተናኮሉኝም ነበር:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምንም ምህረት ሳላሳይ ከንጉሡ የተላከሁ ሀኪም በመሆኔ ሥልጣኔን በመጠቀም የተተናኮለኝ ሰው በአደባባይ ቅጣት እንዲቀበል አጠይቃለሁ:: ቅጣቱም ይፈፀማል:: በዚህ አይነት በካምፑ ውስጥ ለቆሰሉና ለታመሙ ርዳታ እንድሠጥ በንጉሡ የተላከሁ መሆኔን እና ስለኔም ደህንነት ደጃች አያሌው ሀላፊነት የወሰዱ መሆኑን እንዲታወቅ ሆነ:: እንደዚያም ሆኖ በጎሪጥ ነበር የሚያዩኝ ምክንያቱም አቢሲኒያኖቹ በውስጣቸው ሁሉንም ፈረንጆች በጥርጣሬ ማየት ስለጀመሩ ነው::

እኔ ተረድቻቸዋለሁ:: በዚህ ምክንያትም ቂም ሆነ ጥላቻ አልያዝኩም ነገር ግን ያለችኝን በከር የተንጠለጠለች ህይወቴን ለማራዘም እራሴን ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብኝ ብዬ ደጃዝማችን ጠየቅሁ:: ያለውን አደጋ ስለተረዱ ብቻዬን እንደማልወጣ ቃል ገብተው በሄድኩበት ቦታ አብረውኝ የሚሄዱ ሀምሳ ወታደሮች መደቡልኝ::

በዚያው ልክ ደግሞ ብዙ በጦርነቱ ጊዜ ትልቅ እርዳታ ያደረጉልኝ ወዳጆችና ጓደኞችም ነበሩኝ:: ከነዚህ መሀከል አቶ ማሞ ባለቤቱ እና ቤት ውስጥ የተወሰደች የእገልጋይ ልጅ ግን እንደልጅ የሚያሳድጓት የሰምንት አመት ልጅ አፀደን ይጨምራል:: በከፉ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ለኔ ያላደረጉልኝ ነገር የለም በአንድ አጋጣሚም አቶ ማሞ ህይወቴን አድኖልኛል:: እነዚህ ጓደኞቼ ይህንን ቀጥሎ የምፅፈውን መሰመር ቢያነቡ ምኞቴ ነው:: እሱም እነሱ ለሀኪማቸው ላደረጉለት በጎ ነገር ምስጋና እንዳለውና እንደሚገባቸው ለሁልጊዜም የሚያስታውሰው ነገር መሆኑን ነው::

አቶ ማሞ ከአዲስ አበባ በመንግሥት ወደ ደጃዝማች አያሌው በመቶ የሚቆጠሩ የጥይት ጭነቶች እንዲያደርስ የተላከ ሰው ነው:: ባለቤቱም አብራው ተከተለች ቢቆስል ልታስታምመው፣ ቢሞትም ልትቀብር ነው:: ትንሿ አፀደም ሰባት መቶ ኪሎሜትር በእግርዋ ነው የተጓዘችው:: የሚያዞር በሽታ ስላለባት በበቅሎ መሄድ አትችልም ነበር:: ካምፕ ባደረግንበት ቦታ ሁሉ እፀደ እሳት አንድዳ፤ ቡና ቆልታ፤ ፈጭታ ታፈላለች:: በእርሷ ምትክ ቡና

አፈላለሁ ያለ ቢጠነቀቅ ይሻለዋል ምክንያቱም እሷ እንደምታፈላው ቡና የሚሆን የለም ነበር። አፏ ሰፋ ብሎ ከፍርግርግ ጥርሶቿ ጋር ደፍጠጥ ያለ አፍንጫ ያላት የቤት ልጅ ነበረች። ከዚያ በተጨማሪ በጣም ብልህና አሰቂኝም ነበረች። ዘፈን መዝፈንና መወዛወዝ፤ ተረት ማውራት የሚያህላት ለው አልነበረም። ሰውንም ሆነ እንስሳውን አነጋገርና አያያዝ ትችልበታለች። በሚገርሙ ቀልዶቿ በሣቅ እንፈነዳለን። አባባሎቿ ሁሉ የሚገርሙ ነበር (ትንሿ የጦር ጓደኛዬ. ስለአንቺ ሳሰብ አናትሽ እንደምታስብልሽ ሁሉ መጨረሻሽ ምን ይሆን ብዬ አሰባለሁ። አንቺ ትንሽ ጦጣ(በፍቅር አገላለፅ)

አንድ ቀን ህዳር ሁለት ይመስለኛል ከዳባት የተላከ በሰምንት የከብት ጭነት መድሃኒት መጣልን። ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን የተላከ ነበር። ለደጃዝማች ደብዳቤዎች አብረው ተልከዋል፤ ለኔ ግን አልመጣልኝም። በአስር ወራት ውስጥ ከቤተሰቦቼም ሆነ ከጓደኞቼ የሰማሁት ምንም ነገር የለም። ደብዳቤዎቹ እንዲያልፉ ያልተፈቀደበት ምክንያት እስካሁን ድረስ ያልገባኝ እንቆቅልሽ ነው።

በአንደኛው ደብዳቤ ደጃች አያሌውን ተከትዬ እንድሄድ ተፅፎአል። እኔ በነገሩ ልስማማ አልስማማበት ለማወቅ ግን ለማንም ጉዳያቸው አልሆነም። በሚቀጥለው ቀን በደብዳቤው የተፃፈውን የሚያረጋግጥ የቴሌግራም መልከት ተቀበልኩኝ። ከአሁን በኋላ ምን ማድረግ እችላለሁ? በእጃቢ ወደ አዲስ አበባ እንዳልመለስ የማይታስብ ነገር ነው አገሩም መንገዱም አሰተማማኝ አይደለም። ከደጃዝማችም የተሠጠኝ መሳሪያ የለኝም። ደጃዝማች ከሳቸው ጋራ እንድቀርም ስለሚፈልጉ እርዳታ ብጠይቅ እንደሚሠጠኝ ተሰፋ አላደረግሁም።

እንግዲህ ያለሁበት ግንባር እንደሌላው ጦር ግንባር ጥሩም ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም ወደ ጦር ሜዳ እየሄድኩ ነው። ረጋ ባለ መንፈስ ዕጣዬን ተቀበልኩና መዘጋጀት ጀመርኩ። ተዘበራርቀው ተጭነው የመጡት መድሃኒቶች፣ ቁስል መጠቅለያ ጨርቆች እና የህክምና ቁሳቁሶች እየተፈቱ በስም በስም እየሆኑ እንደገና ታሸጉ። ለማንኛውም በቅደም ተከተል ወይም በከብደት አልተስተካከሉም ። ይህ ሥራ ብዙ ቀን ወሰደ ነገር ግን እኔ በፈለግሁት መንገድ ስለተዘጋጅ ደስ ብሎኛል።



ለግሌ የሚሆን ግን የሚረባ ነገር አላዘጋጀሁም። ትንሽ ልብሶች ነው የያዝኩት። ያደረግሁት ጫማም ቢሆን ከሶስት ወር በላይ አያዘልቅም። ወደ አዲስ አበባ ቴሌግራም ልኬ ለአንድ አመት የሚሆን ልብሰና ሌላም አስፈላጊ ነገሮች ያስቀመጥኩበት አረንጓዴው ሣጥን እንዲላከልኝ ጠየቅሁ። ይህንን ሣጥን በሚመለከት በቴሌግራም ሆነ በደብዳቤዎች በመላው ጦርነት ወቅት ልውውጥ ተደርጓል። ሣጥኑ የት እንደደረሰ እስካሁን ድረስ የሚታወቅ ነገር የለም፤ እኔም አላየሁትም።

አብረውኝ እንዲሠሩ የተላኩ ሁለት ተጨማሪ ድሬሰሮች መጡ። ለስምንት አመታት በትሪፖሊ ሆስፒታል የስሩ ናቸው። ፈጠነ የተባለው ሻል ያለውና ጥሩ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያለው በደረጃውም ከፍ ያሰ ስለነበር ዋና ድሬሰር ሆኖ ተመደበ። ለሶስቱም ድሬሰሮቼ እያንዳንዳቸው ምን አይነት የሥራ ምድብ እንዳላቸው መመሪያ ሰጠሁኝ። ከዚያ በተጨማሪ የትኛው ዕቃ ወይ መድሃኒት የትኛው ሣጥን ውስጥ እንዳለ እንዲያጠኑ ተደረገ። ይህም የሚፈለገውን ዕቃ በፍጥነት ለማግኘት እንዲረዳ ነው።

እንደሁኔታውም ቢሆን ሁሉም ነገር በሥነ ሥርአት ተደራጅአቶል ብዬም አሰብኩ፤ ግን የሚበቃ መሣሪያ ስላለነበረኝ ቅር ብሎኛል። በአዲስ አበባ የመሣሪያዎች ዕጥረትም ስለነበር ከጦሩ ሆሰፒታል የሚያስፈልገኝን ቁሰል ማከሚያና መለስተኛ ቀዶ ህክምና ማድረጊያ ስላልወሰድኩ የያዝኩት የግሌን መሣሪያ ብቻ ነበር እንግዲህ ይህ የት ያደርሳል። መንግስት ግን መሣሪያዎች ከአውሮፓ እንደመጡ ወዲያው እንደሚልከልኝ ቃል ተገብቶልኛል።

ሰዎች በእንቅስቃሴ ላይ ስለሆኑ ተጨማሪ ለዎች በየቀኑ ይመጡ ጀመረ። በረጅም መሰመር ተጓዦች፡ የተጫኑ አህዮች፡ በቅሎዎች፡ ፈረሶች በታጠቁ ወታደሮች እየተነዱ ከአገልጋዮች ሴቶችና ልጆች ጋር በመሆን ሲመጡ አየን።

በነጋሪት የከተት ጥሪ የከተማው ሰው ወደ ጦር ሜዳ እንዲዘምት ተጠርቷል። ትልልቅ ግዛት የሚገዛው እያንዳንዱ ራስ ወይም ደጃዝማች የራሱ ነጋሪት አለው በሌላ ከተተካም ነጋሪቱን ለተተኪው እንዲያስረከብ ይደረጋል። ነጋሪት እንደ ግዛቱ ስፋትና እንደ ገዥው ሀይል ከአሥራ ሁለት አስከ አርባ ስምንት በቆዳ የተወጠሩ ከበሮዎች ይኖሩታል። የከበሮዎቹ ሦስት የተለያዩ አይነት መጠኖች ሲኖሩ በቡድን በቡድን በመሆን በተወሰነ ተራ ይጎሸማሉ። እንደ ነጋሪቱ አጎሻሸም ለጦርነት ከተት ጥሪ ወይም በሰላም ጊዜ ወይም ለቀብር ጥሪ ይደረግበታል።

ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ ከበሮዎቹ በበቅሎ ጀርባ ይሆናሉ። በቅሎዎችም

ወይ ሁለት ትንንሽ አለዚያም አንድ ትልቅ ከበሮ ነው የሚጫንባቸው:: ነጋሪት መቺው ደግሞ ከበቅሎው ወደ ጀርባ ወደኋላ ይቀመጣል:: ከበሮው በደንብ ፀሀይ ከሞቀ ፀጥ ባለ አኩስ ቀን እስከ ሀያ ኪሎሜትር ርቀት ድረስ ይሰማል:: ግርማዊ የሆነ ታላቅ ድምፅ አለው::

የነጋሪት ጦር ከተት ሲጠራ መሳሪያ መያዝ የሚችል ማንኛውም ወንድ ባላበት የከተማ ሰው ገበሬ ሳይል ሁሉም ሰው ይመዘገባል:: ቄሶች ብቻ ነው የማይሰለፉት፤ ነገር ግን የቤተከርስቲያን አገልጋይ ካልሆነ በስተቀር የቄስ ልጅ እንኳን ቢሆን አይቀርም :: ብዙ የደረሱ ወንዶች ልጆች ያሉት አባት ከአንድ ልጁ ጋር ብቻ እንዲቀር ይፈቀድለታል:: ባልዋ የሞተባት ሴት ከሆነች ደግሞ አንድ ልጅ ብቻ ካላት ልጁ ከዘመቻ ነፃ ይሆናል ብዙ ልጆች ካሏት ደግሞ አንዱ ብቻ ነፃ ይሆናል::

መሳሪያና ጥይት ደግሞ ራሱ ዘማቹ ነው ማዘጋጀት ያለበት በርግጥ መንግስት ጥይት ያከፋፍላል ነገር ግን የወታደሩ ጥይት ካለቀ በኋላ ነው:: የውጊያ መሣሪያው ደግሞ በየአይነቱ እንደአካባቢውና እንደሰውየው የገንዘብ አቅም ይለያያል:: አንድ ሰው ጠመንጃ ከሌለው ጎራዴውን ይዞ ይወጣል፤ ያም ከሌለው ደግሞ ዱላውን ይዞ ይወጣል:: ግማሹ ወታደር አብዛኛዎቹ የጦር መኮንኖች ከጠምንጃና ሽጉጥ በተጨማሪ ጎራዴ ይታጠቃሉ::

ጎራዴ ረዥም ጠመም ያለ እንደምላጭ ስለት ያለው ብረት ነው:: ከቆዳ በተሠራ አፎት ውስጥ ይደረግና በቀኝ በኩል ከወገብ ላይ በቀበቶ ጠበቅ አድርጎ ይታሰራል:: ሁልጊዜም ቢሆን ይህን መሳሪያ ኢታልዮኖች በጣም ነው የሚፈሩት:: የሚመዘዘው በቀኝ እጅ ወደፊትና ወደላይ በመሳብ ነው:: በአንድ ሥንዝር ብቻ ጠላትን ጭንቅላት እልባ የማድረግ ችሎታ አለው:: ለአቢሲኒያዊው ምርጥ መሳሪያው ነው አጠቃቀሙና አያያዙን ተከኖበታል:: ጎራዴውን የታጠቀ ለታ ወኔው ልክ የለውም:: ያለምንም ውድድር የጀግና ሰው መሣሪያ ነው::

ወታደሮቹ የያዟቸው ጠመንጃዎች ደግሞ የተለያዩ አይነቶች ናቸው:: ጥንታዊው በአፈ ሙዙ ባሩድ የሚጠቀጠቅበት የ1850 አመተ ምህረት ወይም ከዚያ በፊት የተሠራ ሞዴል ነው:: ባሩዱ ከቤት የተሠራ ሲሆን ድንጋይ ወይም የብረት እርሳስ ጋራ ይደባለቃል:: ለመጠቀጠቅም አርጌ ጨርቅ ይጠቀማሉ:: ቢተ መዘከር መቀመጥ የሚገባው ነው:: አንድ ሁለት መቶ

የሚሆኑ የዚህ መሳሪያ አይነቶችን የደጃች አያሌው ወታደሮች ይዘው አይቻለሁ::



በአድሜ ከዚያ ቀጥሎ ሬሚንግተን የሚባል የ1863 ሞዴል ሲሆን ለዚህ መሳሪያም የራሱ ጥይቶች አልተሠሩለትም:: አምስት ከመቶ የሚሆነው የዚህ መሳሪያ አይነት ነው::

በግምት ሰላሳ ከመቶ የሚሆነው ደግሞ በ1870 የተሠራ ፉሲል ግራስ የተባለ የፈረንሳይ 11 ሚሊ ሜትር ካሊበር ጠመንጃ ነው:: ይህም ቢሆን በፋብሪካ የተመረተ ጥይቶች አይጠቀምም ነበር::

የ1880 ሞዴል የሆነ የኢጣልያ ጠመንጃ የራሱ የተመረቱ ጥይቶች የሚኀርስ አይነት ደግሞ ሀያአምስት ከመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይዟል::

ዘመናዊ ከሚባሉት ደግሞ የፈረንሳይ ለበል፤ የእንግሊዝ ሊ መትፎርድ፤ የጀርመን ሞውዜር፤ የአውስትሪያ ማንሊቸር እና የኢጣልያው ሞዴል 91 ይገኙበታል::

የዚህ አይነቱ የተደበላለቀ መሳሪያ አይነት መኖር ደግሞ ትልቅ ችግር አለው እሱም ጥይት ማከፋፈል ላይ ነው:: አንድ የወታደር ቡድን ከላይ የተጠቀሱት የመሳሪያ አይነቶች በሙሉ ሊኖረው ይችላል:: ይህን ችግር ግን ደጃች አያሌው በብልሃት ዘዴ አግኝተውለታል::

እያንዳንዱ ሰው እስከ ጦርነቱ መጨረሻ ድረስ ለራሱ ልብስና ምግብ ሀላፊ ነው:: የወታደር ዩኒፎርም የሚባል ነገር የለም:: ሱሪና ሸሚዝ በላዩ ላይ ሸማ ወይ ኩታ ነው የሚያዘው:: አንድ ተቀያሪ ልብስ፤ ቆርበት፤ ከብርድ ልብስ ጋራ ይያዛል::

በእንቅስቃሴው ወይም በዘመቻው ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ የሚበቃ ምግብ ይሰበሰባል:: የምግብ አይነቶች ደግሞ የሚከተሉት ነበሩ


1. ቆሎ
2. ዳቦ ቆሎ
3. በሶ
4. ጭኮ
5. ሽሮ
6. የጤፍ ዱቄት ለእንጀራ ወይም ለቂጣ መጋገሪያ የሚሆን
7. ሚጥሚጣ ወይም በርበሬ ከሁሉም የምግብ አይነት ጋራ የሚበላ
8. ቡና፣ አሞሌ ጨው
9. የበሬ የበግ ወይም የፍየል ሥጋ ቋንጣ
10. ቅቤና ማር

ይህ ሁሉ ምግብ ከተሰበሰበ በኋላ በስልቻ ይያዛል፡፡ ከቤት ዕቃ ደግሞ የብረት ምጣድ፤ የብረት ድስት፤ የቡና ጀበና፡ የቡና ሙቀጫ፡ መጥረቢያና ማጭድ ይዘናል፡፡ ሌሎች ጥቃቅን የሆኑ እያንዳንዱ ሰው የሚይዛቸው ኢቃዎችም ነበሩ፡፡

ሰባ አምስት ከመቶ የሚሆኑት ወታደሮች ደግሞ የሚጋለብ ጋማ ከብት፤ የጭነት ከብት እንደንብረታቸው መጠን ደግሞ መዝመት የማይገባቸው አጃቢ ሰዎች ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከአጃቢዎች ውስጥ የተገዙ የወንድ አገልጋይ፤ የሴት አገልጋይ ወይም የተቀጠሩ አሽከሮች አሉበት፡፡ ከሰባት አመት በላይ የሆኑ ልጆችም አብረው ዘምተዋል፡፡ የነዚህ ሥራ እንግዲህ ምግብ ማዘጋጀት፤ ውሃ መቅዳት፤ እንስሳቱን መጠበቅ ከሁሉም በላይ ግን የቆሰለ ጌታቸውን መንከባከብ ወይም ሲሞት መቅበር ነው፡፡

ለኔ ግልፅ እንደሆነልኝ አብዛኛው የአቢሲኒያ ሠራዊቱ ቁጥር የተከታዩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሠራዊቱ እንቅስቃሴ ትልቅ እንቅፋት ነው የሆነው፡፡ አውሮፓውያን እንደሚጠብቁት የአቢሲኒያ ሠራዊት ፈጥኖ የሚንቀሳቀስ አይደለም፡፡ ተከታዮችን ወደኋላ ትቶ የሚወጣው ዋናው ጦር ከአውሮፓውያን ሠራዊት የበለጠ የመንቀሳቀስ ችሎታ አለው፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ተንቀሳቃሹ ጦር ለሶስት ቀን የሚሆን ስንቅ ይዞ ነው የሚጓዝው ያ ስንቅም ብዙ ጊዜ ቆሎ ነው፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ ተመልሶ ከተከታዩ ጋራ መደባለቅ የግድ ነው፡፡ ይህ የእንቅስቃሴ ችሎታ የተወሰነ መሆን በጦርነቱ ጊዜ አስከፊ አደጋ ነው ያስከተለው፡፡





ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከግል ዘበኞቻቸው ጋራ ከጦርነቱ በፊት የተነሣ ፎቶግራፍ (ምሥጋና ፋንታሁን ጥሩነህ)

## ምዕራፍ ስድስት

## ውዝግብ

በአዲ አትየ ቆይታችን በመጨረሻዎቹ ሳምንታት ሁኔታዎች በፍጥነት ይካሄዱ ጀመር፡፡ በሰቲት ካሉ የደንበር ጠባቂዎች በመጣ መልከት ሶስት የኢጣልያ አውሮፕላኖች በአምቦ አወታ የሚገኘውን የጫካ ምሽግ በቦምብ መደብደባቸው ተሰማ፡፡ በዚህ ምሽግ ብዛት ያለው የምግብ ሥንቅ የተደበቀበት ቦታ ነበር፡፡ ወደ ስልሳ የሚሆኑ ቦንቦች ተጥለውበታል፡፡ ነገር ግን አንደኛቸውም ቢሆን ግንብ ወይም ቤት ላይ አላረፉም፡፡ ጥቂት ቦምቦች ምሽግ ውስጥ ባለው የውሃ ስፍራ ወደቁ ውሀውም ወደ ቀይ መልከነት ተቀየሮ በውሀው ውስጥ የነበሩ አሳዎችን ገደለ፡፡

የደንበር ጠባቂዎች ደግሞ ውሀውን መጠጣት ይቻል ወይም አይቻል እንደሆነ የኔን ህከምና ዕውቀት በመመርኮዝ ጠየቁኝ፡፡ እኔም በፍፁም ውሀውን እንዳይጠጡ የሚል መልስ ሠጠሁ፡፡ ያ ሁሉ አሳ በአንድ ጊዜ ማለቁ ራሱ ውሀውን ላለመጠቀም በቂ ምክንያት ነበር፡፡ ደጃች አያሌው ሥንቃችን ወደ ገደላማ ቦታዎች ተወስዶ እንዲደበቅ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

ከጎጃም ገዢ ከራስ አምሩ በኩል በመጣ ዜና አርባ ሺ ሰው ይዘው ወደ ጦርነቱ ግንባር እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ተሰማ፡፡ በጣና ሀይቅ ምዕራብ በኩል የሚገኝ ጣቢያ አለፉ ደርሰዋል፡፡ ነገር ግን ወደ የትኛው ግንባር ማለትም ወደ ቆላማው ሰቲት (የሱዳንን ደንበር ይዞ መሄድ) ወይም ደግሞ በሰሜን በኩል ወደ ትግራይ ግንባር የሚሄዱ መሆኑ ግልፅ ስላልሆነ ወደ ጎንደር ተጉዘው ከዛው ሆነው ትዕዛዝ የሚጠብቁ እንደሆነ ተነገረ፡፡

የራስ እምሩ መልከተኞች በቅርብ የማውቃቸው ሁለት ወጣቶች ናቸው፡፡ ከአዲስ አበባ የመጡ ሲሆን፣ የጦር ሠራዊት አገልግሎት ውስጥ ገብተዋል፡፡ የፈረንሳይ ትምህርት ቤት ስለተማሩ ከሌሎች ሠልጠን ያሉ ናቸው፡፡ የለበሱት ልብሰም ጠቆር ያለ ሰማያዊ የሱፍ ልብሰ ነበር የኋላ ኋላ ግን ይህ አለባበስ ለህይወት አሰጊ የሆነ አደጋ ማስከተሉ አልቀረም፡፡ ሁለቱም ሰዎች በተጓዙበት



ባልሠለጠነው የሰሜን መንገዶች ከፍል ገበሬው በስህተት የጣልያን ሰላዮች አድርጎ ያያቸው ነበር፡፡ በዱላ እንዳይደበደቡ ራሳቸውን እየደበቁ መጓዝ ነበረባቸው፡፡ ከመድረሳቸው ከአንድ ቀን በፊት ራሳቸውን ለማዳን ቀጥ ባለ ገደል መውረድ ነበረባቸው፡፡ በዚህ አንገት በሚያሰደፋ ጉዟቸው አንደኛው ከበቅሎ ላይ ወድቆ ሁለት የጎን አጥንቶች ሰብራት ደርሶበታል፡፡ ከሰብራቱ ያልቅ በፍርሀት የተነሳ ሞራሉ ወድቋል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደ ጓደኞቻቸው መልበስ ቢጀምሩ ምክንያቱን መረዳት ይቻላል፡፡

ሕዳር ዘጠኝ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢጣልያ አውሮፕላን ድምፅ ሰማን፡፡ በርቀት መሆን አለበት፡፡ በአይን ማየት አልቻልንም በጠቅላላው ካምፕ ውስጥ ግን ስሜት በመፍጠር የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ፡፡ በሺ የሚቆጠሩት ወታደሮች በጣም ከራቀና ወጣ ካለ ቦታ ስለመጡ ሞተር የሚባል ነገር እንኳን አይተው አያውቁም፡፡

ጥቂቶቹ አውሮፕላኑ አንደ ንብ አይነት ድምፅ ነው ያለው አሉ፡፡ ምናልባትም ለዚህ ይሆናል የሴት ፆታ የሰጡት፡፡ በሰሜን ንብ የሴት ፆታ ነው ያላት፡፡ የኋላ ኋላ አውሮፕላን ቶሎ ቶሎ መታየት ሲጀመር "አሁን መጣች" መባል ተጀመረ፡፡ ቦምብ መጣል ሲጀመር ደግሞ "እንቁላል ጣለች" ይባላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ቀልድ ያለበት አገላለፅ በራሰ አምሩ ሠራዊትም ውስጥ ይነገር እነደነበር በኋላ ጎረቤት ስንሆን ለማወቅ ችያለሁ፡፡

የመጀመሪያ አውሮፕላን በታየችበት ቀን መህመድ ኢማም የሚባል ሰው መጣ፡፡ በጣም ሀብታም አረብ ነው፣ በኤርትራ በሚኖሩ ጣልያኖች ዘንድ የተከበረ ሲሆን በእስልምና አማኞች ዘንድ ደግሞ ታላቅ ተሰሚነት ነበረው፡፡ ምክንያቱም የራሳቸው የነቢዩ መህመድ የትውልድ ሀረግ ስለነበረው ነው፡፡ በደጃች አያሌው ግዛት ውስጥ በንግድ ሥራ ምክንያት ከደጃች አያሌው ጋራ ትውውቅና ወዳጅነትም ነበረው፡፡

ከአራት ቀናት በፊት ስለ ሰውየው መምጣት ሁለት የቴሌግራም መልእከቶች ስለደረሱን አመጣጡ እንግዳ አልሆነብንም፡፡ አንደኛው ቴሌግራም ከአዲስ አበባ ለውየው ወደ ደጃዝማች ካምፕ እንደሚመጣ የሚገልፅ ነው፡፡ እንግዲህ ንጉሡ በሚሰጥራዊ መንገድ በሰሜን በኩል የሚሆነውን እንደሚያውቁ ለማሳወቅም ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሡና መንግሥታቸው በደጃች አያሌው ላይ ሙሉ አምነት እንደሌላቸው ሆኖ ደጃች አያሌው የሚያደርጉትን ነገር በቅርብ እንደሚከታተሉ ለማሳወቅም ነው፡፡

ለዚህ እንግዳ ወደ ደጃች እያሴው መምጣት ጉዳይ በአዲስ አበባ በኩል መታወቁ በኤርትራ ደንበር ያለው የቴሌግራም ኦፐሬተር ነው የተጠረጠረው:: ከዚህ በፊት ለንጉሡ መልክቶችን እንዳሳለፈም ይታወቃል:: ምክንያቱም እሱን ጨምሮ በመላው አገሪቱ ያሉ የቴሌግራም ሠራተኞች ደሞዛቸውን መንግሥት ነበር የሚከፍለው::

ጥርጣሬያችን ግን ስህተት ሆኖ ተገኘ:: ከብዙ ወራት በኋላ እንዳወቅነው የደጃች እያሴው የራሳቸው የጦር መኮንን የደንበር ጠባቂዎች አዛዥ የሆነው ቀኛዝማች መንግስቱ ከንጉሡ ብዙ ብር ተከፍሎት አሲቃውን እየሰለለ ነበር:: የቴሌግራም ሠራተኛው ደግሞ እንደሰማሁት ከሆነ በደጃች እያሴው እየተከፈለው ለሁለቱም ወገን በመሰለል ሥራ ላይ ስለነበረ የንጉሡ ሠላይ ቀኛዝማች መንግስቱ የመሀመድ ኢማምን መምጣት በቴሌግራም ወደ አዲሰ አባባ እንዲያስተላልፍ ፈቀደለት::

ሁለተኛው የደረሰን ቴሌግራም ደግሞ ከአዛዡ ከራሱ ከቀኛዝማች መንግስቱ ነው የነበረው:: በመልክቱም አሲቃውን ሲነግር ባለበት ሀላፊነት መሀመድ ኢማምን ያለ ማለፊያ ወረቀት ድንበር ሲያቋርጥ ስላገኘው እስረኛ አድርጎ ስለያዘው ምን ማድረግ እንዳለበት ከአሲቃው ትዕዛዝ እንዲሰጠው ነው:: ደጃዝማች በአስቸኳይ በቴሌግራም መልሰው እስረኛው ከጠንካራ ጥበቃ ጋር በአስቸኳይ ወደሳቸው እንዲላክ የሚል መልክት ላኩ::

ሰውየው እንደደረሰ ስናየው የተጎሳቆለ ሆኖ ነው ያገኘነው:: ለደጃች እያሴው የሚገባውን ሠላምታ ካቀረበ በኋላ ወድያውኑ ስለደረሰበት በደል ተቃውሞ አሰማ:: የደንበር ጠባቂዎች የነበረውን ዳዝና ንብረት ወሰድውበታል:: የሚለብሰውን የሀር ሸሚዝ እንኳን እንዲለብስ አልፈቀዱለትም:: ለሶስት ቀናት አድርጎት የማያውቀውን በእግሩ እንዲጓዝ መደረጉን፤ ውድ ዋጋ ያለው በቅሎውን እንደተቀማ፤ ምግብ እንኳን ጭብጥ ሙሉ የተቆላ ገብስ ብቻ እንደተሠጠው ከሁሉም በላይ ደግሞ ቡናና ትምባሆ መከልከሉን ተናገረ:: አዘገዙ ደግሞ ጥፋቱ የራሱ የመሀመድ ኢማም እንደሆነ ነገሩት:: ምክንያቱም በጦርነት ጊዜ ያለ ይለፍ ድንበር ማቋረጥ አልነበረበትም:: ቀጥሎም በደረሰበት በደልና ችግር የሚያዝኑ መሆኑን ገልፀው ይቅርታ ጠየቁ:: ለእንግዳው ከዛፍ ስር ድንኳን ከተወጠረ በኋላ ለእንግዳው የሚሆን በግ ባርኮ እንዲያርድ መሀመዳዊ* የሆነ ሰው ተጠራ::

---

*በፀሀፊው አጠራር የነብዩ መሀመድ ተከታዮች በዚያን ጊዜ መሀመዳውያን ተብለው እንደሚጠሩ ነው የሚያሳየው፤ በሌሎች በዚያን ጊዜ የተፃፉ የአውሮፐያን ፅሁፎችም አጠራሩን ሲጠቀሙ ይታያል



የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች በክርስቲያን የታረደ ከብት ሥጋ አይበሉም በአላህና በነቢዩ ደንብ መሠረት ከታረደ ብቻ ነው የሚባለው በዛው ልክ ደግሞ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮችም በሥላሜዎች ሰም ካልተባረከ አይነኩትም:: ቡና በትልቅ መቂያ ላይ ሆኖ ቀረበ እኔም ካለኝ ትምባሆ የማካፈል ከብሩ ደረሰኝ:: ሆኖም እየጎደለ የነበረውን የነበረኝን የትምባሆ መጠን ቀነሰብኝ::

በሚቀጥለው ቀን መሀመድ ኢማምና ደጃች እያሴው ለብቻቸው በመሆን ለረዥም ጊዜ ተነጋገሩ:: ማምሻውኑ ደጃች እያሴው ለኔ በሚስጥር መሀመድ የተላከው ከጓደኛቸው ከኤርትራው ገዢ ጣልያን ነው መልክቱም ደጃዝማች በጦርነቱ እንዳይሳተፉ ለማሳመንና ለመወትወት ነበር:: ደጃች እያሴው ከተስማሙ ጣልያኖች ሲያሸንፉ የራስነት ማዕረግ ተሠጥቷቸው የጠቅላላው የሰሜን ምዕራብ ገዢ ሆነው ሊሾሙ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ብዙ ገንዘብ ስለሚሠጣቸው በሀገሪቱ ውስጥ ትልቅ ሀብታም እንደሚሆኑ ነው::

"እውነት ነው ንጉሡ በድለውኛል" ብለው ደጃዝማች ነገሩኝ:: "ነገር ግን እኔ ሀገሬን በምንም ያህል ገንዘብ የምከዳ አይደለሁም:: ጣልያኖች እኔን ይከዳል ብለው ማሰባቸው የሚያሳፍር ነገር ነው::"

ደጃች እያሴው መሀመድ ኢማምን ምን እንደሚያደርጉት እያሰቡ ነበር:: በርግጥ የጣልያን አምባሰደር ነበር:: ነገር ግን ያለንበትን ካምፕ ለማወቅና ወደፊት እንቅስቃሴያችን ምን እንደሆነ ለማወቅ ተልኮ ቢሆንስ? ስለዚህ እንደ ጦር ምርኮኛ ሆኖ እንዲቆይ ተወሰነና አውሮፕላን ተልኮ ወደ አዲስ አበባ እንዲወሰድ መንግሥት ተጠየቀ:: ቴሌግራሙ ማምሻውኑ ወደ አዲሰ አበባ ተላከ::

ከሁለት ቀን በኋላ የመጣው መልስ ግን እስረኛው በአስቸኳይ ታጅቦ ወደ ደንበሩ እንዲመለስ የሚል ነበር:: ደጃዝማች እያሴውም ሌላ ሰው ሊገነዘብ እንደሚችለው በውሳኔው አልተስማሙም ነገር ግን የግድ ትዕዛዙን ተቀበሉ:: ሰውየውን እንዲሁ መልሶ በነፃ መልቀቅ ያለውን አደጋ እኔም ተረድቻለሁ:: ግን ለትምባሆዬ ስል ቶሎ እንዲሄድልኝ ፈልጌ ነበር::

ስለወደፊት እንቅስቃሴያችን ለሰላዮች የተሣሣተ መረጃ ለመስጠት የማስመሰያ እንቅስቃሴ በማድረግ ካምፑን በትነን መሀመድ ኢማምን ከኛ ጋራ በማድረግ ወደ ሰቲት በሚወሰድው መንገድ ሀያ ኪሎሜትር ገባ ብለን አዲስ ካምፕ መሰረትን:: ከዚህ ተነሰቶም በእጃቢ ወደ ኤርትራ እንዲመለስ ተፈቀደለት::

መሀመድ ኢማም ከኛ ጋር በነበረው ቆይታ ብዙ ጊዜ የአውሮፕላን ድምፅ እንሰማ ነበር፡፡ ጣልያኖቹ የአምባሰደራቸው ሁኔታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ሰማጣራት ተመልካቾች እየላኩ ነበር፡፡

የደጃዝማች አያሌው በንጉሡ ደሰተኛ አለመሆን ምክንያት መነገር የሚገባው ነገር ነው፡፡ ሰብዙ አመታት የደጃች አያሌው ምቀኞች ደጃዝማቹን ከጣልያኖች ጋራ ወዳጅነት ያበዛል እያሉ ለንጉሡ ለአፄ ኃይለ ሥላሤ ነገር ይሰሩባቸው ነበር፡፡ ሆኖም በንጉሡና በደጃዝማቹ መሀከል ላሰው ቀዝቃዛ ግንኙነት ምክንያቱ ይህ ብቻ አልነበረም፡፡

አያሌው ላላቸው ሥልጣንና ማዕረግ ምኒሊክን ነው የሚያመሰግኑት፡፡ ሰለዚህም ከቀድሞ ትውልድ ወገን ነው የሚመደቡት፡፡ አፄ ሀይለ ሥላሤ ዙፋኑን ሲይዙ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን ገሸሸ በማድረግ አብረዋቸው ያደጉ ወጣት ጓደኞቻቸውን ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ይህም የሆነው በከፊል የቀድሞ መኳንንቶችን ባሰማመን ነው፡፡

ይህ ያለመታመን ሁኔታ ሲታወቅ ደጃች አያሌውን በጣም ነው ያስከፋቸው፡፡ ደጃች አያሌው ንጉሡ ሥልጣን ሲይዙ በጣም ነው የረዷቸው፡፡ የምኒሊክ አልጋ ወራሽ ከነበሩት ከልጅ ኢያሱ ጋር በመሀሰ በተደረገው ጦርነት ንጉሡ እንዲያሸንፉ ደጃች አያሌው ከፍተኛ እርዳታ ነው ያደረጉት፡፡ በኋላም ራሰ *ጉግሳ ሲሸፍቱ በ1930 (እኤአ) በአንችም በተደረገው ጦርነት ደጃች አያሌው ናቸው ራሰ ጉግሳን ድል ያደረጉት፡፡ ለዚህ ሥራቸው በንጉሡ እንደ ሽልማት ቃል የተገባላቸው የራሰነት ማዕረግ ተሠጥቷቸው የሰፊው የበጌምድር ገዥ እንደሚሆኑ ነበር፡፡

*ራሰ ጉግሣ ወሌ የእቴጌ ጣይቱ የወንድም ልጅ ናቸው (ጉግሣ ወሌ ብጡል፤ ጣይቱ ብጡል)፡፡ በአንችም በተደረገው ጦርነት ለመጀመሪያ ጊዜ አውሮፕላን በጦርነቱ እንደተሳተፈ ታሪክ ይዘግባል፡፡ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ለመሆን ባላቸውን እንዲፈቱ ተገደው እንደነበረም ታሪክ ይዘግባል፡፡ (ባይሩ ታፍላ ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮጲካ)



ቃል የተገባላቸው ነገር ግን *እውን አልሆነም፡፡ ምናልባትም የደጃች አያሌው እማቻቸው ራሰ ካሳና ሌሎች ቀናተኞች በውሥጥ ለውሥጥ በደጃዝማቹ ላይ ነገር እየሰሩ ሰለነበር ነው፡፡

በተጨማሪ ደግሞ የሳቸው በርቀት ከሚገኘው የሰሜን ግዛት ተነሰተው እንደሌሎቹ እኩዮቻቸው ንጉሡን በየጊዜው እጅ መንሳት አለመቻላቸው ነው፡፡ በንጉሡ ፊት በየጊዜው መቅረብ ደግሞ ለማደግ በጣም አሰፈላጊ ሁኔታ ነበር፡፡

በኔ ግምት ግን ለዳጃች አያሌው መከፋት ዋነኛው ምክንያት ንጉሡ በጠሩት ግብዣ ላይ የተሠጣቸው የመቀመጫ ደረጃ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም መቀመጫቸው ከከፍተኛዎች መኳንንቶች አንዱ እንደመሆኑ በንጉሡ ቀኝ በኩል ይቀመጡ ነበር፡፡ የኋላ የኋላ ግን ያን ሥፍራቸውን ለወጣቶቹ ሰራሰ እምሩና ለራሰ ደሰታ እንዲሰቁ ተደረጉ፡፡ ይህንን ሲያዩ አያሌው ከሰደብ ቆጠሩት "በተሰማኝ ምሬት ምክንያት አንድ ጉርሻ እንኳን በጉሮሮዬ ሊወርድ አልቻሰም" እያሉ ይህ ነገር በተነሣ ቁጥር ያጫውቱኝ ነበር፡፡

ሌላው ምክንያት ደግሞ ለደጃች አያሌው ከማዕከላዊው መንግሰት ጥራት ያላቸው በቂ መሳሪያዎችና ጥይት አለመሰጠት ነበር፡፡ በሌላ ግንባር ያሉ አዛገች ዘመናዊ መውዜር ጠመንጃዎች፣ መትረየሶች፣ የእርሊከን መድፎችና አየር መቃወሚያዎች እንደልባቸው ተሠጥቷቸዋል፡፡

አያሌው ግን አምሰት መቶ መውዜር ጠምንጃዎችና አሰር መትረየሶች ነበር የደረሳቸው፡፡ በራሳቸው ገንዘብ እንኳን 150 መውዜር ከመንግሥት ሲገዙ አሰቸጋሪ ሁኔታ ፈጥረውባቸው ነበር፡፡

*አሁንም በጎንደር "አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" እየተባለ የሚዘፈነው በዚህ ታሪካዊ እውነታ ምክንያት ነው፡፡ ሌሎች ሰለ ደጃች አያሌው የሚገጠሙ ግጥሞች ይህን ይመስላሉ

አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ
የአያል ጠመንጃ ሰሟን እንጃ
አያሌው ለኔ ምንሽሬ ጥሩ አልቢኔ
አያሌውማ የኛ ጥሩ የኛ ዘማ
አያል ተባባል ጎፈሬውስ ያባብላል

የሰፈርንበት ካምፕ በጠገዴና ወልቃይት መለያያ ካላ የሚባል ወንዝ በግምት ወደ አንድ ሺ ሜትር ጥልቀት ባለው ሸለቆ ውስጥ በሚወርድበት ደንበር ላይ ነው፡፡ ወደ ምዕራብ በኩል ሸለቆው ሰፋ ይልና ቆላማና ረባዳ የሆነው የአንገረብ ወንዝ ወደሚፈስበት አቅጣጫ ያመራል፡፡ በምስራቅ በኩል ግን ሸለቆው ድንገት ያቆምና ለጠገዴና ወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶች ተራ ይለቃል፡፡ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ መሬቱ ዝቅ እያለ በመሄድ ከትግራይ ጋራ በተከዜ ወንዝ ከሚለያዩት ወደ ረባዳው ዋልድባና ቆላ ወገራ መሬቶች ይወሰዳል፡፡ የተከዜ ወንዝ በአቢሲኒያ ካሉ ትልቅ ወንዞች አንዱ ነው፡፡ እኛ ደግሞ ቀጥታ ተራራዎችን አቋርጠን ከተራራዎች ማዶ ነበር የምንሄደው፡፡ ቦታው ጠለሎ ይባላል የሰላሳ ኪሎሜትር ርቀትም ነበረው፡፡

በጠዋት የመጀመሪያው የዶሮ ጩኸት (በአቢሲኒያ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ላይ ነው ዶሮ የሚጮኸው) መንገድ ጀመርን፡፡ ሁሉም ነገር ሰላም ከሆነ ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን እንደርሳለን፡፡ በጣም ጥዋት ስለሚሆን የጠላት አውሮፕላኖችንም ለማምለጥ ያመቻል፡፡

አዛዡ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑትን የራሳቸው ጠባቂዎች በማስከተል ከኋላ ሆነው መንገዱን ሲቀጥሉ እኔም በቀጥታ ከእሳቸው ኋላ በመሆን መጓዝ ጀመርን፡፡ ከአንድ ቀን በፊት አንደኛውን ድሬሰር መድሀኒትና መሳሪያዎች ተጭነው ከኛ ፊት ለፊት እንዲጓዙ እንዲያደርግ ሀላፊነት ሰጥቸው ስለነበር ብዙም አልተጨነቅሁም፡፡

በግምት ሁለት ኪሎሜትር መንገድ እንደተጓዝን ሁሉም ነገር ድንገት ቀጥ አለ፡፡ ምን እንዳሰቆመን እንዲያጣራ አንድ ሰው ወደ ፊት ተላከ፡፡ አምስት ደቂቃ ሳይሞላ መልከቱን ሳይጨርስ ተመልሶ መጣ፡፡ ጠባቡ መንገድ በሰዎችና በእንስሶች ስለተጨናነቀ ማለፍ አልቻለም፡፡

ጆሮ የሚያደነቁር ጩኸትና ግርግር ተጀመረ፡፡ እንደዚያም እያለ እስከማታው ድረስ ቀጠለ፡፡ ሁሉም ይጮሃል፤ ከኋላ ያለው ፊት ለፊት ባለው ላይ ሲጮህ የፊት ለፊቱ ደግሞ መልሶ ኋላ ባለው ላይ ሲጮህ ያለምንም ምክንያት ሳይስማማ ለግማሽ ሰአት የሚሆን ሳንንቀሳቀስ ቆመን ቆየን፡፡ በመጨረሻ የችግሩ መንስኤ መድፎቹ መሆናቸውን ጭምጭምታ ሰማን፡፡ ደጃች አያሌው ከራስ ጉግሣ የሠረቋቸው ሁለት የድሮ የተራራ መድፎች አሏቸው፡፡ በ1888 በአድዋ ጦርነት ጊዜም አብረዋቸው ነበሩ፡፡ የማያስተማምኑ አሮጌ እርበኞች እያሉ በቀልድ ይጠሯቸው ነበር ደጃዝማች፡፡ መድፎቹን ፈትቶ በበቅሎ መጫን ይቻላል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ለዚህ ጠባብ



የተራራ ማለፊያ መንገድ ትልቅ ሆነው ተገኙ፡፡ ምን ማድረግ ይቻላል መድፈኞቹ መላውን ሊያገኙለት እንደሚችሉ ተስፋ ማድረግ ነው፡፡



በአንችም በተደረገው ጦርነት የተሸነፉት የንግሥተ ነገሥታት ዘወዲቱ ባለቤት የነበሩት ራስ ጉግሣ ወሌ
(Agenore Frangipani, L'equivoco Abissino)

ከጊዜ በኋላ ችግሩ ተፈታና ጉዞ እንደገና ተጀመረ፡፡ ነገር ግን ያዘገመ በሰአት አንድ ኪሎ ሜትር ብቻ የሚንቀሳቀስ ሆነ፡፡ ቀኑ ሲወጣብን ከኋላ ሆነን የምንጓዘው ሰዎች የሚያስፈራ ትዕይንት ማየት ጀመርን፡፡ መንገዱ ለቀቅ ባለበት ቦታ እንኳን የጎኑ ስፋት ሁለት ሜትር አይሞላም፡፡ በአንድ ጎኑ ቀጥ ያለ የሃምሳ ሜትር ርዝመት ገደል ነው ያለው፤ በሌላ ጎን ደግሞ 500 መቶ ሜትር የሚሆን ቁልቁለት ነው ያለው፡፡ ቁልቁል ስመለከት እኔ ራሴ ሆዴን ቁርጠት ነው የለቀቀብኝ፡፡ እልፎ እልፎ ወንዞ ቦርቡሮ ስንጥቅ ከፍተት ባለበት ቦታ ግንድ ድንጋይና የዛፍ ቅርንጫፎች እንደማለፊያ ተነጥፈውበታል፡፡

በዚህ መንገድ አንድ ላይ የተጨናነቁ ሰዎችና እንሰሳት መሰመር ይዘው አይን ማየት እስከሚችለው ርቀት ድረስ ቀስ ብለው ይጓዛሉ፡፡ አህዮች ሲጓዙ ማየት ራሱ አእምሮን የሚረብሽ ሁኔታ ነው፡፡ እንደ ደንቡ አህዮች ወደ ገደሉ

ጠርዝ በኩል ሆነው ነው እንዲሄዱ የሚደረጉት፡፡ ብዙዎቹ በባለቤቶቹ ኪሳራ የህይወት ዋጋ ነው የከፈሉበት፡፡ አንዱ አህያ ሁለት መቶ ማር ትሬዛ እንደተሜነ ተንከባሎ ከፊት ለፊቴ ወደቀ፡፡

ሙሉ የቀን ብርሃን ስለወጣ ፊት ለፊት ያሉት መንገደኞች መፍጠን ጀምረዋል ሆኖም በቂ አልነበረም፡፡ ሰአቱ እየሮጠብን ነው፡፡ በድንገት የጩኸት ድምፅ እየተቀባበለ እንደሳት ተቀጣጠለ

"መጣች" " መጣች"

ሁሉም ሰው መዝለል፤ ባለበት መቆም ፤ ትንፋሹን መያዝ ጀመረ፡፡ እውነት ነው እየደመቀ የሚመጣ የአውሮፕላን ድምፅ ይሰማኛል፡፡

ደጃዝማች ሁሉም ሰው የየራሱን እንስሳ ይዞ በፀጥታ እንዲቀመጥ እና እንዳይንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ከድምፁ በስተቀር ምንም ሳናይ በመረበሽ መጠበቅ ጀመርን፡፡ እዚህ መሮጫ ሜዳ ወይም መጠለያ በሌለበት ቦታ ላይ ይይዙን ይሆን? መቆረጫ የሌለው የሚመስል ረዥም ጊዜ ከቆየን በኋላ ሁለት ባስነጠላ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች አየን፡፡ ዝቅ ብለው ነበር የሚበሩት፤ እርፈንበት በነበረው የካምፕ ቦታ በኩል አድርገው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሄዱ፡፡

"ምንም ማየት አትችልም! እውር ነች!" በማለት ወታደሮች እርስ በርሰ ይነጋገሩ ነበር መንገዱን እንደገና ስንቀጥል፡፡ በኔ ግምት እነዚህ አልባሌ ጀግኖች የአውሮፕላን ቦምብ አልወረደብንም እና ምን እንደሚመስል እናውቅም ብለው ሳያማርሩ አይቀሩም፡፡

ብዙም ሳንዘገይ ከሰአት በኋላ ጠለሎ(ፀለሎ) ደረስን፡፡ ለሰውም ለእንስሳውም ረዥምና አድካሚ ቁልቁል መንገድ ነበር፡፡ ለዚያን ቀን አድካሚ ጉዞ የመጨረሻው ወይም ማቆሚያችን ነበር፡፡



# ምዕራፍ ሰባት

## ጭስ የሌለው እሳት

ጠለሎ ከባህር ወለል 1800 ሜትር በላይ ይገኛል፡፡ ከዋልድባ ትይዩ በተከዜ ረባዳ ቦታ የመጨረሻው ደንበር ላይ ነው፡፡ የተለያዩ የመሬት ገፅታዎቹ አጠር ካሉ ጫካዎችና ሰፋፊ ሜዳዎች ጋር ያማረና ለካምፓችንም የሚስማማ ሥፍራ አድርጎታል፡፡ ከላይ ከተራራው ተነስቶ የሚወርድ ትንሽ ወራጅ ንፁህና በቂ የመጠጥ ውሃ እንደልብ እንድናገኝ አድርጎናል፡፡

ዕይታው አስደናቂ ነው፡፡ የተከዜን ሸለቆ ማየትም እችላለሁ፡፡ ሸለቆው በደቡብ ምሥራቅ በኩል ከሰሜን ተራሮች ጀርባ ተነስቶ እንደ ትልቅ ገደል እየተጠማዘዘ ወደፊት በመሄድ ፀሀይ በለበለበውና ሰው በማይኖርበት ረባዳ መሬት አድርጎ በሰሜን በኩል በአምባ ብርኩታ ጀርባ ይሰወራል፡፡ ካለንበት በቀጥታ በምሥራቅ በኩል ማዶው የትግራይ መሬት ነው፡፡ በጠራ ቀን በተለይ ከሰአት በኋላ  የአድዋ ተራሮችን መለየት ይቻላል እነሱም በልጅነት ዘመኔ የድሮ ጓደኞቼ ሰሎዳ፣ ሰማይታ እና አባ ገሪማ ናቸው፡፡

የዚህ ሥትራቴጂያዊ አቀማመጥ ጠለሎን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ተነስቶ የወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶችን በመከተል ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰቲት መድረስ ይቻላል፡፡ ይህ አጭር ርቀትም በትግራይ ረባዳ መሬቶች አቋርጦ ሰቲት ከመሄድ ጋራ እኩል ነው፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መንገዶች ወባው መታውቅ የሚገባው አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡

የተከዜ ወንዝ ምንም አይነት እንቅፋት አይፈጥርም፡፡ ወንዙ ጎድሎ ስለነበረ አቋርጦ መሄድ ይቻላል፡፡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ላደረገ ሰውም ከአውሮፕላን ጥቃት መደበቅ የሚቻልባቸው ጥሩ ቦታዎች አሉ፡፡ ሜዳዎችም ቢሆን የሚታጨድ የሚበቃ ሣር ሳላላቸው እንስሶችን ለግጦሽ መልቀቅ አያስፈልግም፡፡

ሌላው የጠለሎ ራቅ ብሎ መገኘት ጥቅም ደግሞ የኢጣልያ አውሮፕላኖች በየቦታው ቢበሩም ያተኮሩት ካርታ ላይ በሠፈሩት መንገዶች ላይ ነው፡፡